# የክርስቶስ ቤዝሆት

---------

---------

---------

# PENAL SUBSTITUTION ATONEMENT



# PREPARED BY: MERE-PROTESTANTISM

**JOIN US ON TELEGRAM: @MERE_PROTESTANTISM**

# መግቢያ

በዚህ ፅሁፍ ውስጥ በአራት ክፍሎች ስለ ክርስቶስ ቤዝሆት ስራ እንመለከታለን። በመጀመሪያው ክፍል፡ የክርስቶስ ቤዝሆት ምንነት፣ ቲዎሪዎች ና ታሪክ፤ በሁለተኛው ክፍል የቤዝሆት አስፈላጊነት፤ በሶስተኛው ክፍል የምትካዊ ቅጣት ቤዝሆት መፅሀፍ ቅዱሳዊ መሠረት በስተመጨረሻም በአራተኛው ክፍል ምትካዊ ቅጣት ቤዝሆት ላይ የሚቀርቡ ትችቶች ና መልሶቻቸው በሚል እናያለን።

ስለ ክርስቶስ ቤዝሆት ቲዎሪዎች አዲስ ለሆኑ አንባቢያን እንዲሆን በሚል አንዳንድ ነገሮችን ከስር መሠረቱ ለማሳየት ተሞክሯል። በአስተውሎት ላነበበ ሰው ከሁሉም ቲዎሪዎች መካከል አንዳንዶቹ የተመሠረቱበት ስርወ-ሃሳብ ትክክል ላይሆን ቢችልም እንኳን ሁሉም ግን በውስጣቸው የያዙት መፅሃፍ ቅዱሳዊ እውነት እንዳለ ማየት ይቻላል። ስለዚህ አንዱ አንዱን የሚቃወም ና የሚጣረስ አድርጎ ከማቅረብ ይልቅ እርስ በእርስ እንዲያያዙ በማድረግ የክርስቶስን ድንቅ የማዳን ስራ ማሳየት እንደሚቻል ለማሳየት ተሞክሯል። በተለይ ከቤዝሆት ቲዎሪዎች መካከል ብዙ ጊዜ የሚገፋውን ና ትምህርቱን በሚቀበሉትም ውስጥ አግባብ የሌለው አጠቃቀም የሚስተዋልበትን የምትካዊ ቅጣት (ወይም ምትክ ተቀጪ) ቲዎሪ ምንነቱን፣ መፅሃፍ ቅዱሳዊ መሠረቱን ና ታሪካዊ ማስረጃዎቹን ለማሳየት ሞክረናል። የሚነሱበትንም ጥያቄዎች ለመመለስ ሞክረናል። ይህ የምትካዊ ቅጣት ቲዎሪ ከመገፋት ይልቅ ሌሎቹን ቲዎሪዎች ሳንጥል ነገርግን በማዕከላዊነት ልንጠቀምበት የሚገባ ቲዎሪ መሆኑን ይህም የመፅሀፍ ቅዱስ አቀራረብ መሆኑን ለማሳየት ሞክረናል።

በአጠቃላይ በፅሁፉ የምናስቀምጠው መሠረታዊ ሃሳብ የክርስቶስ የማዳን ስራ በትክክል ይገለፅ ዘንድ ሁሉም የቤዝሆት ቲዎሪች በአንድ ላይ መቀናጀት እንዳለባቸው በዚህ ውስጥ ደግሞ ሁሉን አቃፊ እንደመሆኑ የምትካዊ ቅጣት [Penal substitution] ቲዎሪ ማዕከላዊ በታውን [centrality] መያዝ እንዳለበት ነው።

# ክፍል-1-- የቤዝሆት ምንነት፣ ቲዎሪዎች ና ታሪክ

## ቤዝሆት [Atonement] ምን ማለት ነው?

ቤዝሆት የሚለው የእንግሊዘኛ ቃል Atonement ሲሆን At - one – ment ከሚለው ስርወ-ቃል የመጣ ነው። ትርጓሜው ወደ አንድነት መምጣት ወይም ማስታረቅ ማለት ነው። ከዚህ እንደምንረዳው ቤዝሆት የክርስትና ማዕከላዊ ነጥብ ነው። የክርስቶስ ቤዛነት ካለንበት የኃጢያት ማጥ ተላቀን ከእግዚአብሄር ጋር የታረቅንበት፣ ልጁ ተደርገን የተቆጠርንበት ነውና ቤዝሆትን መረዳት አስፈላጊነቱ አጠያያቂ አይደለም። ክላሲካል የሆነው ክርስትና 'ክርስቶስ አዳኛችን ነው ወይ?' በሚለው ላይ ውዝግብ ብዙ ተፈትኖ አያውቅም። ይልቁንስ በክርስትና ውስጥ ክርክሮች ሲደረጉ የነበሩት 'ክርስቶስ እንዴት አዳነን?' በሚለው ላይ ነበር እንጂ 'ክርስቶስ አዳኝ ነው ወይ?' በሚለው አልነበረም። ክርስቶስ እንዴት አዳነን ለሚለው የሚሰጡ የተለያዩ መልሶችን የቤዝሆት ቲዎሪዎች ብለን እንጠራቸዋለን።

# THEORIES OF ATONEMENT

### ክርስቶስ እንዴት ቤዛ ሆነን?

የሉተራኑ ቲዎሎጂያን Gustaf Aulén ስራ ከሆነው 'Christus victor' መፅሀፍ በኋላ የቤዝሆት ፅንሰ ሃሳቦች በሰስት ዋና ዋና ክፍሎች ተከፍለው መታየት ጀምረዋል። ይህም ክፍፍል ቲዎሪዎቹ ቤዝሆቱን ከምን ጋር እንደሚያገናኙት በማጤን የሚደረግ ነው፡

1. ከሰይጣን ጋር [Satanward] ካለው ግንኙነት አንፃር [Christus victor, classical or dramatic theory]: በዚህ ውስጥ Christus victor ቲዎሪ ና በእርሱ ውስጥ የሚካተተው Ransom ቲዎሪን ማንሳት እንችላለን።
2. ከእግዚአብሄር ህግ ጋር ካለው ግንኙነት አንፃር [objective or legal theory]፡ Satisfaction theory ና Penal substitution atonement ያካትታል።
3. ከግለሰብ ጋር ካለው ግንኙነት አንፃር [Subjective theory]: Moral influence theory ና Example theory ያካትታል።

በመቀጠል እነዚህ ቲዎሪዎች የሚያቀርቡትን ሃሳብ በዝርዝር እናያለን።

## A. የክርስቶስ አሸናፊነት ቲዎሪ [Christus Victor[1] Theory]፡

ይህ ቲዎሪ ቤዝሆት ከክርስቶስ አሸናፊነት ጋር የሚያገናኝ ነው ይላል። ክርስቶስ የሞተበት ምክንያት ገዝቶን ከነበረው ከጨለማው አለም ነፃ ሊያወጣን ነው። ማለትም ሰው በኃጢያት ሲወድቅ ለሰይጣን፣ ለጨለማ ና ለአለም ተገዢ ባርያ የሆነ ሲሆን ክርስቶስም ሰው በመሆኑ፣ በህይወቱ፣ በአገልግሎቱ ና በሞቱ ባሪያ ካደረጉን ከእነዚህ ሃይላት ነፃ አውጥቶናል። ሃሳቡ በዋናነት ከሰው የኃጢያት *ተጠያቂነት [responsibility]* ይልቅ የሰው የኃጢያት *ተጠቂነት [victim]* ላይ ትኩረት ያደረገ ነው። ለምሳሌ ከዘመኑ የዚህ ቲዎሪ አቀንቃኞች መካከል አንዱ የሆኑት ግሬግ በይድ ሲናገሩ እንዲህ አስቀምጠውታል፡ It is arguably for this reason that Paul does not see "sin" first and foremost as a matter of individual behavior, as most modern Westerners do. He rather conceives of "sin" (and related concepts such as the "law" and the "flesh") as a quasi-autonomous power that holds people groups as well as individuals in bondage.[2]

በዚህ ቲዎሪ መሠረት የሰው መሠረታዊ ችግር ባሪያ አድርገው የያዙት የአለም ሃይላት ናቸው። ሰው መዳን ካለበትም መዳን ያለበት ከእነዚህ ሃይላት ነው። ስለዚህ ክርስቶስ በመስቀሉ የሰራው እነዚህን ሃይላት ማሸነፍ ነው። *እነርሱ ሲያስቀምጡትም አመክንዮዋዊ በሆነ ቅደም ተከተል [Logical priority] የአለም መዳን ከግለሰብ መዳን ይቀድማል።* ይህም ማለት እኛ የዳነው ክርስቶስ አለምን ስላሸነፈ ብቻ ነው። በቦይድ ቃል፡ the cosmic significance of Christ's work is ontologically more fundamental than its soteriological significance…We are reconciled because the cosmos has been reconciled. [3]

ይህ ቲዎሪ ብዙ ጊዜ ችግር ውስጥ የሚገባው *'ክርስቶስ እንዴት ከስሞሱን አሸነፈ?'* ለሚለው መልስ ለመስጠት ሲሞክር ነው። በዚህ መሠረት በቤተክርስቲያን ታሪክ ውስጥ ሲሰነዘሩ የነበሩ አንዳንድ በዚህ ቲዎሪ ስር የሚካተቱ ሞዴሎችን እንይ፡

**The Ransom Theory** [4]**:** ይህ ክርስቶስ በሞቱ የሰራው ትልቁ ስራ እኛን ከሰይጣን ባርነት ማስለቀቅ ነው ብሎ በሚያስበው ቲዎሪ (Christus victor theory) ውስጥ የሚሰነዘር ሀሳብ ሲሆን የሀሳቡ ጠንሳሽ ግን የቀደምት ቤተክርስቲያን ሊቁ ኦሪገን[Origen] ነው። ኦሪገን እንደሚለው እግዚአብሄር እኛን ከባርነት ለማስለቀቅ ለሰይጣን ካሳ [ransom] ከፍሏል። ይህም ካሳ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። ሰይጣን የሰው ልጆችን ከያዘበት ባርነት ይልቅ ዘንድ የጠየቀው ካሳ የኢየሱስን ደም ሲሆን እርሱም ያሰበው በዚህ ሰበብ ኢየሱስን በእጁ ለማስገባት ነበረ። ነገርግን ኢየሱስንም መያዝ ሳይችል የቀደሙትንም ባሪያዎቹን አጥቶ ባዶ እጁን በመቅረት በክርስቶስ ድል ተደረገ ይላል፡

---

[1] Christus victor is Latin for 'Christ the victor' (ክርስቶስ አሸናፊው)

[2] The Nature of the atonement four views

[3] Ibid

[4] Ransom = the price of release (የማስለቀቂያ ክፍያ ማለት ነው።)

"To whom did he [Christ] give his life a ransom for many? Assuredly not to God; could it then be to the evil one? For he was holding us fast until the ransom should be given him, even the life of Jesus; being deceived with the idea that he could have dominion over it, and not seeing that he could not bear the torture in retaining it."[5]

ከዚህ በኋላ ይህን ሃሳብ አሳድጎ ሲያቀርብ የምናገኘው ጎርጎሪዮስ ዘኑሲስ ሲሆን እርሱ ደግሞ እግዚአብሄር ሰይጣንን እንደሸወደው (እንደቆመረበት [bait]) ይገልፃል። ይህም በክርስቶስ ሰውነት ውስጥ መለኮት መኖሩን በመደበቅ ነው። ሰይጣን የኢየሱስን መለኮትነት ባለማስተዋሉ ኢየሱስን ማሸነፍ ና በቁጥጥሩ ስር ማዋል እንደማይከብደው እርግጠኛ ነበረ። ይህም ቸልተኝነቱ እንዲሸነፍ አድርጎታል። በጎርጎርዮስ ቃል፡

In order to secure that the ransom on our behalf might be easily accepted by him [Satan] who required it, the deity [of Christ] was hidden under the veil of our [human] nature. Thus, as with ravenous [hungry] sh, the hook of the deity might be gulped down along with the bait of esh. In this way, life would be introduced into the house of death, and light would shine in the darkness. And so that which is diametrically opposed to light and life might vanish; for it is not in the nature of darkness to remain when light is present, or of death to exist when life is active.[6]

ይህ የክርስቶስ አሸናፊነት ቲዎሪ በላቲን አባቶች ዘንድ ደግሞ የሚቀርብበት መንገድ ትንሽ ለየት ያለ ነው። አንዳንዶች ይህንን *ፖለቲካል ሞዴል* ብለው ይጠሩታል። ይህ ሞዴል ልክ እንደ ራንሰም ሞዴል ክርስቶስ የሞተው እኛን ከሰይጣን አገዛዝ ለማስለቀቅ ነው የሚለውን ይቀበልና ነገርግን እግዚአብሄር ለሰይጣን ክርስቶስን ከፈለ የሚለውን አይቀበልም። እነርሱ እንደሚሉት ኢየሱስ የሰይጣን ተጠቂ [Victim] ነበረ። ሰይጣን ሰዎችን ሁሉ በኃጢያት ምክንያት የመግደል ሙሉ ስልጣን ቢኖረውም ክርስቶስ ግን ከኃጢያት ንፁህ ነበረና እርሱ ላይ ኢ-ፍትሃዊ ሆኗል። ይህ ኢ-ፍትሃዊነቱም እግዚአብሄር በክርስቶስ በኩል ሰዎችን እንዲያፀድቅ ምክንያት ሆኖታል። ታላቁ አባት አውግስጢኖስ በዚህ ላይ ሲፅፍ፡

Because, when he found in Him nothing worthy of death, yet he slew Him. And certainly it is just, that we whom he held as debtors, should be dismissed free by believing in Him whom he slew without any debt. In this way it is that we are said to be justified in the blood of Christ. For so that innocent blood was shed for the remission of our sins. [7](On the Trinity 13.14.18)

ኢየሱስ ለሰይጣን የተከፈለ ክፍያ ነው የሚለው ሃሳብ ያልጣማቸው የቤተክርስቲያን አባቶችም ነበሩ። ከእነዚህም መካከል ዩሀንስ የደማስቆው አንዱ ሲሆን እርሱ እንደሚለው የኢየሱስ ሞት ክፍያ ቢሆንም ነገርግን የተከፈለው ለሰይጣን ሳይሆን ለእግዚአብሄር ነው። እግዚአብሄርም በክርስቶስ መለኮትነት

---

[5] Origen, Commentary on Matthew 16:8

[6] The Great Catechism 24

[7] On the Trinity 13.14.18

የሸወደው ሰይጣንን ሳይሆን ሞትን ነው። ሞት ኢየሱስን ይዞ ማስቀረት የሚችል መስሎት ነበረ ነገርግን እርሱ መለኮት ነውና ሞትን አሸነፈ። እንዲህ ፅፏል፡

he took on himself death on our behalf, and he makes himself an offering to the Father for our sakes. For we had sinned against him, and it was right that he should receive the ransom for us, and that we should thus be delivered from the condemnation. God forbid that the blood of the Lord should have been offered to the tyrant. Therefore, death approaches and, swallowing up the body as a bait is transfixed on the hook of divinity, and after tasting of a sinless and life-giving body, perishes, and brings up again all whom of old he swallowed up. For just as darkness disappears on the introduction of light, so is death repulsed before the assault of life, and brings life to all, but death to the destroyer."[8]

የክርስቶስ አሸናፊነት ቲዎሪ የራሱ ጠንካራ ና ደካማ ጎኖች አሉት፡

- ✓ ጥንካሬው፡ በመጀመሪያ የክርስቶስን ማዳን ከሁሉም የክርስቶስ የህይወት ክፍል ጋር አያይዞ ማቅረቡ ነው። ክርስቶስ መወለዱ፣ ህይወቱ፣ አገልግሎቱ፣ ሞቱ ና ትንሳኤው ሁሉ በዚህ ቲዎሪ ከድነት ጋር ተቆራኝተው በጥሩ መልኩ ቀርበዋል። ሁለተኛ ብዙ ጊዜ በምዕራባውያን ነገረ-መለኮት ላይ የሚዘነጋውን ክርስቶስ በኮስሞስ ሃይላት ላይ ያስመዘገበው ድል ና ይህ አሸናፊነቱ በሚገባ ትኩረት የተሰጠበት ነው። ይህ ደግሞ ወርቃማ የመፅሃፍ ቅዱስ እውነት ስለሆነ ይበል የሚያሰኝ ነው። (ቆላ 2፡15፣ ሐዋ10፡38, ሉቃ 11:21-22…)
- ✓ ድክመቱ፡ ሰውን የኃጢያት ተጠቂ ብቻ በማድረግ ተጠያቂነቱን ገለል ማድረጉ ነው። ኃጢያት የፈቃዳችን ውጤት የሆነ ና የእግዚአብሄርን ቁጣ የሚቀሰቀስ መሆኑ ትኩረት አልተሰጠበትም። ይህ ደግሞ የቲዎሪውን ሃሳብ ሙሉ በሙሉ ሌላ መልክ አስይዞታል። በተጨማሪም የሚያስቀምጠው አመክንዮዋዊው ቅደም ተከተሉ ትክክል አይመስልም። ምክንያቱም ሰው ለኮስሞስ ሃይላት ለመገዛቱ ምክንያቱ ኃጢያት ነበረ ካልን ለመዳን ምክንያት መሆን ያለበት ከኃጢያት መላቀቅ እንጂ ከሃይላቱ መላቀቅ አይደለም። ስለዚህ የክርስቶስ የማዳን ተግባር ከማሸነፍ ተግባሩ አመክንዮዋዊ ቀደምትነት ያለው ነው።

## B. ምትካዊ ቅጣት (PENAL SUBSTITUTION VIEW)

ይህ የቤዝሆት ምልከታ እንደሚለው እግዚአብሄር የወደቀውን ሰው ሞት ና እርግማን ለማስወገድ በልጁ በክርስቶስ ኢየሱስ አማካይነት የሰው ልጆች ምትክ ሆኖ የኃጢያት ቅጣትን እርሱም ሞትን ተቀብሏል። ሰው ሁሉ ኃጢያትን ሰርቷል የእግዚአብሄርም ክብር ጎድሎታል። (ሮሜ3፡23) የኃጢያት ቅጣት ደግሞ ሞት ነው። (ሮሜ6፡23) የእግዚአብሄር ቅዱስ ቁጣ በኃጢያተኞች ላይ ነዷል። (ሮሜ1፡18) ክርስቶስ ሲሞት የእኛን ኃጢያት ና እርግማን ተሸክሞ ና የኃጢያታችንን ቅጣት ተቀብሎ በመሆኑ (2ቆሮ5፡21፣ ገላ3፡10) እኛ

[8] John of Damascus, Exposition of the Orthodox Faith, 3.27

የኃጢያት ይቅርታን አግኝተናል። ክርስቶስ የእግዚአብሄር ፍትህ የሚጠይቀውን ሁሉ በሟሟላት ምትካችን ሆኖ የእግዚአብሄርን ቁጣ አብርዷል [Propitiation]። ይህም ብቻ አይደለም ባፈሰሰው ደም ኃጢያታችንን አጥቧል [Expiation]።

በዚህ ቲዎሪ ውስጥ ግልጥ መሆን ያለባቸው ቃላት አሉ፡

1. ምትክነት [Substitution]፡ ማለት መሞት የሚገባው ኖሮ፤ መኖር የሚገባው ሲሞት ማለት ነው። ይህ ሃሳብ የሚመዘዘው ከብሉይ ኪዳን መስዋዕት የማቅረብ ስርዐት ነው። በብሉይ ኪዳን መስዋዕት ሲቀርብ በኃጢያኛው ቦታ የሚሞት በግ ወይም አንዳች ሌላ እንስሳ ይዘጋጃል። በጉ ለኃጢያተኛው ቅያሪ ወይም ምትክ ነው። በኃጢያተኛው ላይ መድረስ የነበረበት በበጉ ላይ ይደርሳል። መኖር የሚገባው በግ ይሞታል፤ መሞት የሚገባው ኃጢያተኛ ግን በህይወት ይኖራል። ክርስቶስ የእኛ ምትክ ነው ስንል እያልን ያለነው መሞት የሚገባን እኛ የምንኖረው መኖር የሚገባው የእግዚአብሄር በግ በእኛ ቦታ ስለተቀየረ ነው። ይህን ሃሳብ ቲ. ጄ. ክራውፎርድ በጥሩ ቃል ገልፀውታል፡

‘The text, then, according to its plain and obvious import, teaches the vicarious nature of the rite of sacrifice. Life was given for life, the life of the victim for the life of the offerer’, indeed ‘the life of the innocent victim for the life of the sinful offerer’[9]

ይህን ለመግልፅ አንዳንዶች ምትክ [substitution] ከሚለው ይልክ ተወካይ ወይም ውክልና [representative] የሚል ቃልን ይመርጣሉ። ጄ.አይ. ፓከር በእነዚህ መካከል ልዩነት እንደሌለ ይልቁንስ ተመሳሳይ ሃሳብን እንደሚገልፁ ያስረዳሉ። እሳቸው እንደሚሉት ጳውሎስ ምትክነትን ለመግለፅ የተጠቀመባቸው ሁለት የግሪክ ቃላት ***[hyper, anti]*** በምንም ቃል ብንገልፀው ክርስቶስ ምትካችን መሆኑን እንዳንክድ ያደርጉናል። [ሮሜ5፡8፣ ገላ3፡13፣ ማር10፡45]

2. ቅጣት [Penal][10]፡ ማለት በኃጢያት ላይ የሚወርድ የእግዚአብሄር ቁጣ ነው። መፅሀፍ እንደሚል የኃጢያት ደመወዝ (ቅጣት) ሞት ነው። ሞት የሚለው ቃል ቀጥተኛ ትርጉሙ ‘መለየት [separation]’ ማለት ነው። ይህ ሞት የስጋ ወይም የመንፈስ ሞትን ሊያመለክት ይችላል። የስጋ ሞት የነፍስ ከስጋ መለየትን ሲያመለክት የመንፈስ ሞት ደግሞ የመንፈስ ከእግዚአብሄር መለየትን ያመለክታል። ክርስቶስ በመስቀሉ የእኛን ኃጢያት ተሸክሞ ሲወጣ ይህን የኃጢያት ቅጣት ስለ እኛ ተቀብሏል። ክርስቶስ ከሚመጣው የእግዚአብሄር ቁጣ አድኖናል፡ ..***ከሙታንም ያስነሳውን ልጁን እርሱንም ኢየሱስን ከሚመጣው ቍጣ የሚያድነንን ከሰማይ ትጠብቁ ዘንድ..*** (1ተሰ1፡10)

[9] T. J. Crawford, Doctrine of Holy Scripture, pp.237, 241
[10] ‘penal’ being derived from poena, a penalty or punishment.

3. ስርየት [Expiation]፡ የአማኙ ከኃጢያት መንፃትን የሚያመለክት ነው። በብሉይ ኪዳን የእንስሳት መስዋዕት የምንመለከተው ትልቁ ነገርም ይህንን ነው፤ መስዋዕት የሚቀርበው ሰዎችን ከኃጢያት ለማንፃት ነው። የቃሉ ትርጉም የሚያመለክተው *ወደ ሰው* ነው።
4. የቁጣ መብረድ [Propitiation]፡ በብሉይ ኪዳን በዕብራይስጡ *'kapha'* ተብሎ በአዲስ ኪዳን ደግሞ በግሪኩ *'hilasterion'* በሚል ቃል የተገለጠ ሲሆን ትርጉሙ በእግዚአብሄር ፊት የሚቀርብን ማስተሰረያ ያመለክታል። (ዘሌ 4፡35፣ 10፡17፣ 16፡30) በአንድ መልኩ ማስተሰረያ በመሆኑ ስርየትን የሚያመለክት ሲሆን በእግዚአብሄር ፊት መቅረቡ ደግሞ እግዚአብሄር ለኃጢያት የሚሰጠውን ምላሽ ይህም ቁጣውን ለማብረድ የሚደረግ መሆኑን ያሳያል። ስለዚህ የቃሉ ትርጉም የሚያመለክተው *ወደ እግዚአብሄር* ነው።

እነዚህን ሃሳቦች ሰብስበን በድጋሚ የምትካዊ ቅጣት ቤዝሆት ምንድነው የሚለውን ብናይ እንዲህ እናስቀምጠዋለን፡ ***ክርስቶስ ኢየሱስ ስለ እኛ ምትክ ሆኖ ከኃጢያታችን መታጠብን እንዲሁም የእግዚአብሄርን ቁጣ በመቀበል በመስቀል ላይ በሞተ ጊዜ ለእኛ ምህረትን አስገኝቶልናል።***

የዚህ ቲዎሪ ጥንካሬ ና ድክመቶች በአጭሩ፡

- ጥንካሬ፡
  - ✓ *የእግዚአብሄርን ባህርያት ያማከለ እና ሚዛናዊነት የሞላበት ነው።* እግዚአብሄር ፍቅር ነው፤ ደግሞም ቅዱስ ነው! በእነዚህ ሁለት የእግዚአብሄር ፍፁም ባህርያት መካከል ትልቅ አጣብቂኝነት [dilemma] አለ። ይህ ቲዎሪ እግዚአብሄር ሁለቱንም ባህርያቱን ጠብቆ እንዴት እንዳዳነን በሚገባ የሚገልፅልን ነው። በኋላ ይህን በደንብ አብራራዋለሁ።
  - ✓ *ኃጢያትን መፅሀፍ ቅዱሳዊ በሆነው ህጋዊ መልኩ ማቅረቡ ትልቅ ጥንካሬ ነው።* በዚህም ድነታችን ግንኙነታዊ ገፅታ [relational aspect] ብቻ ሳይሆን ህጋዊ ገፅታ [legal aspect] ያለው መሆኑን በሚገባ ይገልፃል። ሌሎች ቲዎሪዎች ግንኙነታዊ መልኩን ቢያሳዩንም ነገርግን ህጋዊ መልኩ ደምቆ የሚታየው በምትካዊ ቅጣት ቲዎሪ ነው።
  - ✓ *የቤዝሆትን አመክንዮዋዊ ቅደም ተከተል በሚገባ የጠበቀ ነው።* በዚህ ቲዎሪ መሠረት የክርስቶስ መስቀል ቅድሚያ ያስታረቀው እግዚአብሄርን ከአለም ጋር [Objective nature of the atonement] ሲሆን በመቀጠል አለምን ከእግዚአብሄር ጋር [Subjective nature of the atonement] አስታርቋል ። የመጀመሪያ ተፅዕኖው የእግዚአብሄርን ቁጣ ማብረድ ሲሆን በመቀጠል ና <u>በዚህ ምክንያት</u> የአለምን ሃይላት አሸንፏል፣ ጨለማን ገፏል!! ስለዚህ ከክርስቶስ አሸናፊነት ቲዎሪ በተለየ መልኩ የክርስቶስ የማዳን ተግባር አለምን ከማሸነፉ አመክንዮዋዊ ቀደምትነት አለው የሚለውን አፅንኦት ይሰጣል።
  - ✓ *የኃጢያትን አስከፊነት [gravity of sin] ና የእግዚአብሄርን ተመጣጣኝ የሆነ ፍርድ [retributive justice] በሚገባ ተዋቅረው የሚገለፁበት ነው።*
  - ✓ *ክርስቶስ ከእግዚአብሄር ቁጣ እንዳዳነን ለሚናገሩ የመፅሀፍ ቅዱስ ክፍሎች ታማኝ ነው።* 1ተሰ1፡10 ፣ ሮሜ 5፡9

- ✓ *ሥላሴያዊ ና ክርስቶሳዊ መሆኑ፡ በአብ በወልድ ና በመንፈስ ቅዱስ መካከል ያለው የፈቃድ አንድነት በሚገባ የሚንፀባረቅበት ነው።*
- ✓ *ሁሉንም የቤዝሆት ቲዎሪዎች ያቀፈ ነው።* ምትካዊ ቅጣት ቲዎሪ የክርስቶስ አሸናፊነትን እንዲሁም በኋላ የምናነሳቸውን የምሳሌነት ቲዎሪዎች.. ወዘተ ሁሉ መግለፅ የሚችል ሁሉን አቃፊ ነው። ለዚህም ይመስላል ጄ.አይ. ፓከር ምትካዊ ቅጣትን እንደ ቲዎሪ ሳይሆን እንደ ቤዝሆት ትርጉም መቅረብ ያለበት ነው የሚሉት። "it important for the theory of penal substitution to be evaluated as a model setting forth the meaning of the atonement rather than its mechanics."[11]

- ➢ ድክመቱ፡
  - ✓ ለብቻው እንዲቆም ካደረግነው ድነትን በክርስቶስ ሞት ላይ ብቻ በጣም ያተኮረ እንደሆነ እንድናስብ ያደርገናል። የክርስቶስ ህይወቱ፣ አገልግሎቱ፣ ትንሳኤው ሌሎች ቲዎሪዎች ላይ እንደሚታየው ድምቅ ብለው አይታዩም። ይህ ማለት ግን ቲዎሪው ከሞቱ ውጪ ያሉት የክርስቶስ የህይወት ክፍሎች ለድነት አያስፈልጉም ይላል ለማለት ሳይሆን ብዙ ጊዜ አይነገርላቸውም ለማለት ነው።

ሁለቱን በብዙዎች ዘንድ ተቀባይነት ያላቸውን ቲዎሪዎች ከተመለከትን የቀሩትን ቲዎሪዎች ደግሞ የቤዝሆት ታሪክን ስናጠና አካትቼ አቀርባለሁ።

# History and Theories of Atonement

የቀደመችው ቤተክርስቲያን ከነገረ-ክርስቶስ አስተምሮ ውስጥ ከክርስቶስ ስራዎች [Works of Christ][12] ይልቅ የክርስቶስ ማንነት [Person of Christ] ላይ ብዙ ስትሰራ ቆይታለች። ይህም ኑፋቄዎች ብዙውን ጊዜ ያነጣጠሩት የክርስቶስ ማንነት ላይ መሆኑን ተከትሎ ነው። በክርስቶስ የመስቀል የቤዝሆት ስራ ላይ ቤተክርስቲያን ጉባኤ አዘጋጅታ አታውቅም፤ አባቶችም የተለየ ትኩረት ሰጥተው ይህን ጉዳይ አንስተው አያውቁም። ስለዚህም በቤተክርስቲያን አባቶች ዘንድ የተለያዩ የቤዝሆት እሳቤዎች ና አቀራረቦችን እንመለከታለን። ይህን ስንመለከት አባቶች በስርየት ላይ ባላቸው ፅንሰ ሃሳብ ትልቅ ስምምነት ነበራቸው ብለን መናገር አንችልም። የተለያዩ ሃሳቦችን ያነሳሉ፤ ከሚያነሱት መካከልም አንዱ የምትካዊ ቅጣት ቲዎሪን ነው። ወደ ቀደምት አባቶች ከመሄዳችን በፊት በተወሰነ ቅጣት ምትክነት በአንሰልም ና በሪፎርመሮቹ የተገለጠበትን መንገድ እንዲሁም ከእነርሱ ተቃራኒ የነበሩ ምልከታዎችን እንመልከት፡

## የአንሰልም ቲዎሪ [Satisfaction theory]፡

---

[11] Logic of penal substitution J.I. Packer

[12] በተወሰነ መልኩ በአትናቴዎስ በእንተ-ተሠግዎተ ቃል ስራ ላይ የሚታይ ቢሆንም ለመጀመሪያ ጊዜ በክርስቶስ ቤዝሆት ስራ ላይ የተሰራ ሰፊ ስራ በቤተክርስቲያን ታሪክ የምናገኘው የአንሰልም "አምላክ ለምን ሰው ሆነ?" የሚለውን መፅሀፍ ነው። ይህ በራሱ ጉዳዩ በቤተክርስቲያን ታሪክ ለረጅም ጊዜ ትልቅ ቦታ እንዳልተሰጠው ማሳያ ነው።

ቅዱስ አንሰልም የካተርቤሪው የ11ኛው ምዕተ-አመት ክርስቲያን አሳቢ ሲሆን በአጠቃላይ ሶስት አጫጭር ነገርግን እጅግ ጠቃሚ ስራዎችን ያበረከተ ሊቅ ነው። ስራዎቹም፡ Monologion፣ Proslogion ና Cur Deus Homo? የሚባሉ ነበሩ። ከእነዚህ መካከል ሁለተኛው ለእግዚአብሄር ህልውና ኦንቶሎጂካል ሙግት [Ontological argument] ያቀረበበት ታዋቂ ስራው ሲሆን የመጨረሻው መፅሀፉ ደግሞ 'እግዚአብሄር ለምን ሰው ሆነ?' በሚል ሀሳቦችን ያቀረበበት ድንቅ ስራው ነው።

የአንሰልምን ሃሳብ በሚገባ ለመረዳት አንሰልም ይኖርበት የነበረው ዘመን ፊውዳል ሲስተም በጥቂቱ ማወቅ ሊጠቅመን ይችላል። ይህ ሲስተም ህዝቡን ጌታ ና ባሪያ በሚል በመክፈል ስልጣን የሚተገበርበት ዘመን ነበረ። ጌቶች የባሮቻቸውን ደንነት ማስጠበቅ ትልቁ ስራቸው ሲሆን ባሮች ደግሞ ጌቶቻቸውን የመመገብ ና የማገልገል ሃላፊነት ነበረባቸው። በዚህ መሰረት አንድ ባሪያ ጌታውን ሰርቆ ቢገኝ ግን ለቅጣቱ ተገቢውን *የሚያረካ* ቅጣት [Satisfaction] መቀጣት ይገባዋል የሚል አሰራር ነበረ። ለምሳሌ፡ 2 በጎችን የሰረቀ እንደሆነ 2 በጎችን ብቻ ቢመልስ ተገቢ ካሳ አይሆንም ምክንያቱም የሰረቃቸውን በጎች ቢመልስም በስርቆት ያዋረደውን የጌታውን ክብር [Honor] ግን አልካሰም። ስለዚህ ካሳው የተሰረቀውን የሚመልስ ብቻ ሳይሆን የተጎጂውን ክብርን የሚክስ መሆን አለበት። እንደ ምሳሌ 2 ሰርቆ እንሆነ 5 መመለስ ሊኖርበት ይችላል።

አንሰልም "ኃጢያት መስራት ከእግዚአብሄር በመስረቅ የእግዚአብሄርን ክብር ማዋረድ [dishonoring God] እንዲሁም ለእርሱ የሚገባውን አለመስጠት ነው" ይላል። በዚህም ምክንያት የኃጢያት ይቅርታን ለማግኘት ብቸኛው መንገድ ይህ የእግዚአብሄር ክብር በሚያረካ መስዋዕት ሲካስ ነው ይላል። ለምሳሌ እንዲህ ፅፏል፡

To sin is nothing other than not to give God what is owed to him. What is the debt which we owe to God? ... This is righteousness or uprightness of the will. It makes individuals righteous or upright in their heart, that is, their will. This is the sole honor, the complete honor, which we owe to God and which God demands from us.... Someone who does not render to God this honor due to him is taking away from God what is his, and dishonoring God, and this is what it is to sin.[13]

እግዚአብሄር ይህ የተወሰደበት ክብሩ ሳይመለስለት እንዲሁ በባዶ ሜዳ ምህረት አያደርግም። እርሱ ያለው ሁለት ምርጫ ነው፡ አንድ ይህ ክብሩ እንዲመለስለት ማድረግ ካልሆነ ደግሞ አጥፊዎቹን መቅጣት። አንሰልም እንደሚለው ሰውን ሁሉ መቅጣት ለእግዚአብሄር የማይታሰብ ነው። ምክንያቱም በሰይጣን መሪነት የወደቁ መላዕክትን ቁጥር ያህል የሚሆኑ ሰዎች መዳን አለባቸው ይላል። በዚህ እግዚአብሄር የተዛባውን የአለም ስርአት ይመልሳል ብሎ ያምናል። በመቀጠልም አንሰልም የሚያነሳው ይህን የእግዚአብሄርን ክብር ማን በሚያረካ መልኩ ሊክስ ይችላል? የሚል ሃሳብን ሲሆን ይህን ለማድረግ ሰው በአዳም ሃጢያት በመውደቁ እንደማይችል ካነሳ በኋላ ያለው ብቸኛ አማራጭ ከፋዩ እራሱ እግዚአብሄር መሆን እንዳለበት ነገርግን ለሰው ውድቀት አምላክ መክፈሉ ተገቢ ስለማይሆን ይህ ከፋይ ሰውም መሆን

[13] Why God Became Man, 1.11

እንዳለበት ነው። ስለዚህ ትክክለኛ የእግዚአብሄርን ክብር የሚክስ መስዋዕት መቅረብ የሚችለው አምላክም ሰውም [God-Man] በሆነ አካል እንሆነ ያነሳል።

But the obligation rests with man, and no one else, to make the payment…. Otherwise mankind is not making recompense. If, therefore, … no one can pay except God, and no one ought to pay except man: it is necessary that a God-man should pay it. [14]

አንሰልም በዚህ ረገድ በሶስት ነገሮች የበለፀገ ቲዎሪን ሰንዝሯል፡

- ✓ የኃጢያትን አስከፊነት በሚገባ አሳቷል
- ✓ የእግዚአብሄርን ቅድስና በሚገባ አሳይቷል
- ✓ የክርስቶስን ፍፁም መስዋዕት መሆንን አሳይቷል

ነገርግን አንዳንዶች እንደሚሉት የአንሰልም ቲዎሪ በፊውዳል ና በህጋዊ ስርአት የታወረ ቲዎሪ አይደለም። ዶ/ር ጋቪን በቲዎሎጂካል ሪትሪቫል መፅሀፋቸው እንዳሳዩት አንሰልም በመፅሀፉ በተደጋጋሚ ከጥንት ከሄራኒዎስ የነበረውን የሪካፕቹሌሽን ቲዎሪ [Recapitulation theory] የሚመስሉ በርካታ ሃሳቦችን ያነሳል። ለምሳሌ፡

“It was fitting that just as death entered the human race through the disobedience of a human being, so too life should be restored by the obedience of a human being.”[15]

ይህ የአንሰልም የቤዝዎት ፅንሰ ሃሳብ በወቅቱ በብዙዎች ዘንድ ተቀባይነት ያገኘ ቢሆንም አንዳንድ ተቃውሞዎችም ነበሩበት። ከእነዚህ መካከል፡

- ➢ አቤላርድ የተባለው የፓሪሱ የምግባር ተፅዕኖ ፅንሰ ሃሳብ [Moral-influence theory] ጠንሳሽ አንዱ ነበረ። እርሱ እንደሚለው እግዚአብሄር ያለ ክርስቶስ መከራ አለምን እንዲሁ በንሰሃ ብቻ ማዳን ይችል ነበር። ክርስቶስ የተወለደበትም ሆነ የሞተበት ምክንያት ትልቅ ፍቅሩን ለመግለጥ ና እኛም በዚህ ፍቅር ውስጥ እንድንቀሳቀስ ተፅዕኖ የሚፈጥር ምሳሌ ሊሆነን እንጂ የምትክነት ዕቅድ ይዞ አይደለም። በዚህ መንገድ አቤላርድ የመስቀሉ ስራ ከግለሰብ ተፅዕኖው አንፃር [Subjective influence of the cross] አብራርቶታል። የዚህ ምልከታ ትልቁ ድክመት ግን ክርስቶስ ለእኛ የሰራውን ክርስቶስ በእኛ ከሚሰራው ጋር ለይቶ አለማስቀመጡ ነው።
- ➢ በርናርድ የክሌርቫክሱ ደግሞ በዚያው ዘመን የክርስቶስ አሸናፊነት ቲዎሪ ክፍል የሆነውን ራንሰም ቲዎሪን ማስተማሩን ቀጥሎበት ነበረ።

## ሪፎርመሮቹ ና ከእነርሱ በኋላ፡

---

[14] Ibid 2.6

[15] Ibid 1.3

በሪፎርመሮቹ ሲቀነቀን የነበረው የቤዝዎት ፅንሰ ሃሳብ የቅጣት ምትክነት [Penal substitution] የሚባለው ነው። ይህ ሃሳብ በብዙ መንገዶች ከአንሰልም ሃሳብ [satisfaction theory] ጋር ተመሳሳይ ቢሆንም ነገርግን ከአንሰልም የሚለየው ቤዝዎቱን የሚያገናኘው ከእግዚአብሄር ክብር መደፈር [Honor of God] ጋር ሳይሆን ከእግዚአብሄር ፍትህ [Justice of God] ጋር መሆኑ ነው። እግዚአብሄር ቅዱስ ነውና ኃጢያትን ያለምንም ቅጣት በምህረት ብቻ ሊያልፍ አይችልም። የኃጢያት ደመወዝ ሞት ነው እንደሚል ቅዱስ መፅሀፍ ይህንን ቅጣት የሚከፍል ያስፈልጋል። ክርስቶስ በእኛ ቦታ የእኛን ቅጣት የተቀበለ አዳኛችን ነበረ። በዚህም እግዚአብሄር ስርየትን መስጠት ብቻ ሳይሆን በኃጢያት ላይ የነበረውን ቁጣም ክርስቶስ ላይ ገልጧል። በሪፎርመሮቹ መካከል በዚህ ጉዳይ ሙሉ ስምምነት የነበረ ቢሆንም ልዩነቶች የነበሩት 'ይህ ቤዝዎት ለማን ነው?' [Extent of the atonement] በሚለው ላይ ብቻ ነበረ። በሪፎርምዱ ወገን ያሉት ለተመረጡት [for the elected] ሲሉ በሉተራኑ ወገን ያሉት ደግሞ ለአለም ሁሉ ብለዋል። በኋላም ከሪፎርምዱ ወገን ቤዝዎቱ ለአለም ሁሉ ነው ያሉ በጃኮብ አርሚኒየስ የሚመራ ቡድን ተነስቷል።

ከሪፎርመሮቹ በኋላ የእነርሱን ሃሳብ በመቃወም የመጡ ሁለት ሰዎች ነበሩ፡

- ✓ የመጀመሪያው ዩኒቴሪያኑ ፋውስተስ ሶሲነስ [Faustus Socinus] ነው። የእርሱ የቤዝዎት ቲዎሪ ምሳሌያዊ ቲዎሪ [Example Theory] የሚባለው ነው። እርሱ እንደሚለው እግዚአብሄር መሃሪ ከሆነ ፍትሃዊ ሊሆን አይችልም። ማለትም ምህረቱን ለመስጠት ፍትሃዊነቱን መተው አለበት። ለእግዚአብሄር ምህረትን ወይም ፍትህን መስጠት የነፃ ፈቃዱ ውጤት ነው እንጂ የባህርይው ግዳጅ አይደለም። ስለዚህ በፈቃዱ ከሁለት አንዱን ይመርጣል እንጂ ሁለቱንም በአንድ ጊዜ መተግበር አይችልም። ይህ የሶስያኒዝም ትምህርት ክርስቶስ በእግዚአብሄር ሃይል የታጠቀ ብቻ እንጂ ከእግዚአብሄር ጋር እኩል ነበረ ብሎ አያስተምርም (ሥላሴን የሚክድ ኑፋቄ ነው) በዚህም ክርስቶስ በህይወቱ ና በሞቱ ያሳየን በምን አይነት ምግባር እግዚአብሄርን መከተል እንዳለብን ብቻ ነው። ሞቱ ምትክነት ሳይሆን ምሳሌነት ብቻ ነው ይላል። ይህ ቀደም ብለን ካየነው የአቤላርድ ምግባር ተፅዕኖ ቲዎሪ ጋር በተወሰነ ያመሳስለዋል።
- ✓ ሁለተኛው ሁጎ ግሮቲየስ (17ኛው ክፍለ ዘመን) የሚባል ሰው ሲሆን ከሪፎርመሮቹም ሆነ ከሶሲያኒዝም የተለየ ሀሳብን ያንፀባረቀ ነበር። በአንድ በኩል የሶሲያኒዝሞቹ እግዚአብሄር ከፍትሁ ምህረቱን መርጦ ፍትሁን ተወ የሚለውን መቀበል አልፈለገም፤ በሌላ በኩል ደግሞ የሪፎርመሮቹን ክርስቶስ የእግዚአብሄርን ቁጣ አበረደ የሚለውንም መቀበል አልፈለገም። እርሱ እንደሚለው እግዚአብሄር የህግ ሰጪ እንጂ የህግ ተገዢ አይደለም። በዚህም ህጉን በፈለገው ጊዜ ማላላት ና ማጥበቅ [relaxation of the law] ይችላል። በክርስቶስ ሞት እግዚአብሄር የገለጠው ታዲያ ኃጢያትን ሳይቀጣ እንደማያልፍ ብቻ ነው። ይህም ማለት ክርስቶስ የሞተው የኃጢያት እዳን ሙሉ በሙሉ ለመክፈል ሳይሆን ኃጢያት በእግዚአብሄር ፊት የሚቀሰቅሰውን ቁጣ ለማሳየት ብቻ ነው።ግሮቲየስ እግዚአብሄርን እንደ ዳኛ አድርጎ ከማየት ይልቅ እንደ መሪ [Governer] ያየዋል። እንደ መሪነቱም ዋነኛ አላማው የአለምን ምግባራዊ ስርዐት [Moral order

of the world] ማስጠበቅ በመሆኑ ክርስቶስም የሞተው ለዚሁ አላማ እንደሆነ አፅንኦት ይሰጣል። በዚህ ምክንያት የግሮቲየስ ቲዎሪ **Governmental theory** ተብሎ ይጠራል።

# PSA in Church Fathers:

ከምትካዊ ቅጣት የቤዝሆት አስተምሮ ተቃዋሚዎች መካከል የብዙዎቹ ድክመት ከቤተክርስቲያን ታሪክ ምንም ድጋፍ የሌለው አድርገው ማቅረባቸው ነው። ነገርግን ማስረጃዎችን ዘር ዘር ብሎ ለፈለገ ይህ እውነት ሆኖ አይገኝም። ትልቁ ነጥብ ከላይ እንዳነሳነው በቀደሞቸው ቤተክርስቲያን የስርየት ጉዳይ ብዙ የጭቅጭቅ መንስኤ አልነበረም። በዚህም በአባቶች ዘንድ ጥርት ያሉ አመለካከቶችን አናገኝም። እንደዚህ ባለበት ሁኔታ አባቶች የኔን ትምህርት ብቻ ነው ያስተማሩት ማለት የሚችል የለም። በአንድ አባት ፅሁፎች ላይም ወጥ የሆነ ምልከታን ማግኘት ያስቸግራል። ቀጥሎ በፅሁፎቻቸው ስለ ቅጣት ምትክነት ያስተማሩ የቤተክርስቲያን አባቶችን/ፀሀፊዎችን በጥቂቱ አነሳለሁ፡

- ✓ ቀለምንጦስ፡ "Christ bore our in iquities and suffered for our sakes. He was wounded for our transgressions and bruised for our sins."[16]
- ✓ አውሳብዮስ፡ The Lamb of God . . . was chastised on our behalf, and suffered a penalty He did not owe, but which we owed because of the multitude of our sins; and so He became the cause of the forgiveness of our sins, because He received death for us, and transferred to Himself the scourging, the insults, and the dishonour, which were due to us, and drew down on Himself the apportioned curse, being made a curse for us. And what is that but the price of our souls? And so the oracle says in our person: "By his stripes we were healed," and "The Lord delivered him for our sins."[17]
- ✓ ኦሪገን፡ "God pre-determined him as a propitiation through faith in his blood." This means of course that through the sacrifice of himself he would make God propitious to men. . . . For God is just, and the one who is just could not justify the unjust; for that reason he wanted there to be the mediation of a propitiator so that those who were not able to be justified through their own works might be justified through faith in him.[18]
- ✓ ዩሀንስ አፈወርቅ፡ "For all the outrages which we heaped on Him in return for His benefits, He not only did not punish us, but gave us His Son. He made Him to be sin for us —that is, He allowed Him to be condemned as a sinner and die as one accursed. He made Him to be a sinner and sin, who, far from having 5 committed sin, knew no guile"[19]

---

[16] First Epistle of Clement, ch 16
[17] Demonstration of the Gospel 10.1
[18] Commentary on the Epistle to the Romans 3.8.1
[19] Homilies on II Corinthians, homily 11

እንዲሁ በሌላ ቦታ

"A king, beholding a robber and malefactor under punishment, gave his well-beloved son, his only-begotten and true, to be slain; and transferred the death and the guilt as well, from him to his son, (who was himself of no such character), that he might both save the condemned man and clear him from his evil reputation"[20]

- ✓ አውግስጢኖስ፡ As He died in the flesh which He took in bearing our punishment, so also, while ever blessed in His own righteousness, He was cursed for our offenses, in the death which He suffered in bearing our punishment. . . . The believer in the true doctrine of the gospel will understand that Christ is not reproached by Moses when he speaks of Him as cursed, not in His divine majesty, but as hanging on the tree as our substitute, bearing our punishment. (Against Faustus 14.6–7)

  "[W]e came to death through sin; he [Christ came to it] through righteousness: and, therefore, as our death is the punishment of sin, so his death was made a sacrifice for sin."[21]

  እንዲሁ በሌላ ቦታ

  Christ, though guiltless, took our punishment, that he might cancel our guilt, and do away with our punishment.... Confess that he died, and you may also confess that he, without taking our sin, took its punishment.[22]

- ✓ ቅዱስ አትናቴዎስ፡ It was necessary that the debt owed by everyone should be paid, and this debt owed was that everyone should die. For this particular reason, Jesus Christ came among us.... He offered up his sacrifice on behalf of everyone, yielding his temple [i.e., his body] to death in the place of everyone.... And so it was that two wonderful things came to pass at once: the death of everyone was accomplished in the Lord's body, and death and corruption were completely done away with by reason of the Word that was united with it. For death was necessary, and death must be suffered on behalf of everyone, so that the debt owed by everyone might be paid[23]

- ✓ ጎርጎርዮስ ዘናዚአንዘስ፡ As for my sake He was called a curse, Who destroyed my curse; and sin, who taketh away the sin of the world; and became a new Adam to take the place of the old, just so He makes my disobedience His own as Head of the whole body. As long then as I am disobedient and rebellious, both by denial of God and by my passions, so long Christ also is called disobedient on my account.[24]

---

[20] Homilies on II Corinthians, homily 1

[21] On the Trinity 4.12.15

[22] Reply to Faustus the Manichaean, 14:4, 7

[23] On the Incarnation of the Word, 20

[24] Gregory of Nazianzus, The Fourth Theological Oration , in Nicene and Post - Nicene Fathers, ser. II, vol. 7

# ትክክለኛ የቤዝሆት ቲዎሪ የቱ ነው?

ብዙ ጊዜ ትክክል ያልሆነ ጥያቄ፡ ***“የትኛውን የቤዝሆት ቲዎሪ ነው የምትቀበለው?”*** የሚለው ነው። አነሰም በዛ ሁሉንም ቲዎሪዎች መቀበል አለብን። የክርስቶስ አሸናፊነት ቲዎሪ፣ የምትካዊ ቅጣት ቲዎሪ፣ ምሳሌያዊ ቲዎሪዎች ሁለቱም መፅሀፍ ቅዱሳዊ መሆናቸውን ተመልክተናል። ለምሳሌ በቤዛነቱ ክርስቶስ ከኃጢያት አንፅቶናል ከእግዚአብሄር ቁጣ አድኖናል ብቻ ሳይሆን አለምን ና ሰይጣንን አሸንፏል እንላለን። የክርስቶስ ቤዛነት በአንድ ቲዎሪ ብቻ የሚወሰን ሳይሆን ብዙ መልክ ያለው [Multi-faceted] ነው። ስለዚህ ይህን ቲዎሪ ብቻ ነው የምቀበለው ማለት በራሱ ስህተት ነው። ሙግቱ መሆን ያለበት የክርስቶስ ቤዛሆት ማዕከላዊ ተግባሩ ምንድነው? ወይም በሌላ ቋንቋ ሁሉንም ቲዎሪዎች አቅፎ የሚይዝልን ቲዎሪ የትኛው ነው? የሚለውን ላይ ነው።

ከዚህ አንፃር ምትካዊ ቅጣት [Penal substitution] ቲዎሪ የክርስቶስ የማዳን ስራ ላይ ማዕከላዊ ቦታ እንደሚይዝ ማየቱ ያስፈልጋል። ይህም ማለት ሁሉንም ቲዎሪዎች ማቀፍ የሚችል በመሆኑ በዚህ ቲዎሪ አማካይነት ሌሎቹን ቲዎሪዎች ማብራራት እንችላለን። ለምሳሌ

- ✓ ክርስቶስ ምትክ ሆኖልን ኃጢያታችንን ተሸክሞ በመስቀል ኃጢያታችንን ሲያነፃ ለሰይጣን ና ለአለም ባሪያ ያደረገንን ኃጢያትን ከላያችን አስወገደው። በዚህም እኛ ነፃ ወጣን። ስለዚህ የክርስቶስ ምትካዊ ቅጣት ለክርስቶስ አሸናፊነት እንደ ምክንያት ነው። አለምን ያሸነፈው ኃጢያታችንን ስላስወገደ ነው።
- ✓ ይህም ብቻ አይደለም መስቀሉ ላይ የተገለጠው ፍቅር የተገዛንበት ፍቅር ነው። ሐዋሪያው እንደሚለው ፡ **እርሱ አስቀድሞ ወዶናልና እኛ እንወደዋለን** (1ዩሀ44፥19) ለመውደዳችን ምክንያቱ መወደዳችን ነው። ይህ ፍቅር ደግሞ ለክርስቶስ ለመኖር ያለን ቁርጠኝነት እርሱንም ምሳሌ አድርጎ ለመኖር የሚያስችለንን መሰጠት የሚያመጣ ነው። ስለዚህ ምትካዊ ቅጣት ቲዎሪ የአቤላርዱን ምግባር ተፅዕኖም ሆነ የሶሲነሱን ምሳሌያዊ ሞዴል በውስጡ የሚይዝ ነው።

ከዚህ የምንገነዘበው ምትካዊ ቅጣት ቲዎሪ የክርስቶስ አሸናፊነት ቲዎሪ ጋር ወይም ሌሎች ካየናቸው ቤዝሆቱን ከግለሰብ አንፃር ከሚያብራሩት ቲዎሪዎች ጋር በተቃራኒ የሚቆም ሳይሆን እንደውም ማዕከል አድርገን ከያዝነው ሁሉን ማቀፍ ና ማብራራት የሚችል ቲዎሪ መሆኑን ነው። አሁን ግን እንዳለመታደል ሆኖ ሰዎች እንኳን ማዕከላዊ ሊያደርጉት ጥቃት እያደረሱበት ና እየካዱት የሚገኙት ቲዎሪ ሆኗል።

# ክፍል-2

# ቤዝሆት ያስፈልገናል? [Necessity of the Atonement]

በዚህ ላይ ሶስት አይነት ሀሳቦች ይሰነዘራሉ፡

1. ***ስርየት ጭራሽ አያስፈልገንም የሚሉ፡*** በዚህ ውስጥ የምናገኛቸው በፔላጂያን እርሾ የተላወሱትን ና ደንነት በሰው አቅም ያለ እግዚአብሄር ፀጋ ይገኛል የሚሉትን ነው። ከዚህ በተጨማሪ የ16ኛው ምዕተ-አመት ሶሲያኒዝም ና የዘመኑን ሊበራል ቲዎሎጂም በዚህ ውስጥ የሚካተቱ ይመስላል። በአጠቃላይ እነዚህ ኢየሱስ ለኃጢያት ሳይሆን ለምሳሌነት ብቻ እንደሞተ የሚያስቡ ናቸው።
2. ***ስርየት አስፈላጊ ነው ነገርግን ግዴታ አይደለም የሚሉ [hypothetically necessary]፡*** ይህ ምልከታ ደግሞ እግዚአብሄር በመስቀሉ ማዳንን መረጠ እንጂ ለማዳን ከክርስቶስ ሞት ውጪ ብዙ አማራጮች ነበሩት የሚል ነው። ድነትን ለመስጠት የክርስቶስ መሞት የእግዚአብሄር ነፃ ምርጫ እንጂ ብቸኛ አማራጩ አልነበረም። እግዚአብሄር ሁሉን ቻይ እንደመሆኑ በሌላ መንገድም ቢሆን ሰዎችን ማዳን ይችል ነበር። ይህን ምልከታ እንደ አውግስጢኖስ ና ቶማስ አኳይናስ ባሉ ትላልቅ የቤተክርስቲያን ሰዎች ዘንድ የምናገኘው ነው።
3. ***ስርየት ግዴታ አስፈላጊ ነው የሚሉ [absolute necessity]፡*** እግዚአብሄር አለሙን ለማዳን የክርስቶስን ሞት የመረጠው ከዚህ ውጪ አማራጭ ስላልነበረው ነው። ሃሳቡ እግዚአብሄር አለምን የማዳን ግዴታ አለበት የሚል ሳይሆን አለምን ለማዳን የወደደ አምላክ ያድነው ዘንድ ስጋ ለብሶ መሞት ነበረበት የሚል ነው። ይህ በብዙ ፕሮቴስታንቶች ዘንድ የሚታመን ነው።

## እግዚአብሄር ከቤዝሆት ውጪ አማራጭ ነበረው?

*ፃድቁ እግዚአብሄር ፅድቁን ጠብቆ ሌሎችን ያፀድቅ ዘንድ* ቤዝሆቱ መፈፀሙ የግድ ነበረ። ክርስቶስ እንደዛ ተሰቃይቶ የሞተው አለሙን ለማዳን የመስቀል ጉዞው ብቸኛ አማራጭ ስለነበረ እንጂ የህይወት ተሞክሮ ለማግኘት አይደለም። እንደዛማ ቢሆን ***"ብትፈቅድ ይህችን ጽዋ ከእኔ ውሰድ"***(ሉቃ22፡42) ባለ ጊዜ አባት ሁሉ ነገር ትቶ ሌላ የማዳን እቅዱን [plan B] በተጠቀመ ነበር። እግዚአብሄር ምህረት ለማድረግ ለምን የቤዝሆት ስራው ግዴታ ሆነ ካልን ግን ባለፈው ምዕራፍ ባየነው መሠረት ብዙ ምላሾች ይሰጣሉ። አንዳንዶች ከሰይጣን ጋር ባለው ግንኙነት ሲያስቀምጡት ሌሎች ከህግ ጋር ሌሎች ደግሞ ከአለም ምግባራዊ ስርዐት ጋር ያገናኙታል። በእነዚህ ሁሉ ውስጥ ግን ጥንቃቄ የሚፈልገው እግዚአብሄርን ለሌሎች ውጫዊ ነገሮች ተገዢ እንዳናደርገው ነው። የትኛውም ውጫዊ ነገር እግዚአብሄርን አንዳች ነገር እንዲያደርግ ሊያስገድደው አይችልምና። የእግዚአብሄር ድርጊቶች ሁሉ የሚወጡት ከውስጥ ባህርይው እንጂ ከውጫዊ ሃይሎች አይደለም። በዚህም ቤዝሆት ሰዎችን ለማዳን ግዴታ ነበረ ስንል ያለ ቤዝዎት የእግዚአብሄር የውስጥ ባህርይ ተጠብቆ (ሳይለወጥ) እኛ መፅደቅ አንችልም እያልን ነው። ስለዚህ ግዴታነቱ ውስጣዊ እንጂ

ውጫዊ አይደለም [Intrinsic necessity]። በዚህ ላይ ሂድል በርግ ካቴኪዝም 40ኛው ጥያቄ ላይ እንዲህ ይላል፡

Q. Why did Christ have to suffer death?

A. Because God's justice and truth require it: nothing else could pay for our sins except the death of the Son of God.

ነገሮችን ከመሠረታቸው ስንመረምር ቤዝዎት ያስፈልገናል ወይ? ለሚለው ጥያቄ የምንሰጠው መልስ የሚመሰረተው በሁለት ነገሮች ላይ ባለን አመለካከት ነው። የመጀመሪያው 'ኃጢያት ምንድነው?' የሚለው ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ'እግዚአብሄር ማነው?' ወይም 'የእግዚአብሄር ባህሪያት ምንድናቸው?' የሚለው ነው። የኃጢያት ምንነት ና አግዚአብሄር በባህርይው ለኃጢያት የሚሰጠውን ምላሽ በአግባቡ ካልተረዳን ስለ ቤዝዎት ያለን አመለካከት ትክክል ሊሆን አይችልም። ጆን ስቶት በዚህ ጉዳይ ሲናገሩ እንዲህ ይላሉ፡

All inadequate doctrines of the atonement are due to inadequate doctrines of God and man. If we bring God down to our level and raise ourselves to his, then of course we see no need for a radical salvation, let alone for a radical atonement to secure it. When, on the other hand, we have glimpsed the blinding glory of the holiness of God, and have been so convicted of our sin by the Holy Spirit that we tremble before God and acknowledge what we are, namely 'hell-deserving sinners', then and only then does the necessity of the cross appear so obvious that we are astonished we never saw it before.[25]

ስለዚህ ቀጥለን ስለ ስለ ኃጢያት ና ስለ እግዚአብሄርን ባህሪያት የተወሰኑ ነጥቦችን እንመልከት፡

# 1. ኃጢያት ምንድነው?

ሐዋሪያው ዩሀንስ አጠር ያለ መልስ ይሰጠናል፡ "**ኃጢያት ዓመፅ ነው፡፡**" 1ዩሀ3፡4 ኃጢያት ህግን መተላለፍ ነው፤ ህግን አለማክበር ነው። እንግዲህ በዘመኑ ቋንቋ ህግ መተላለፍን ዓመፃ ከሚለው ይልቅ ወንጀል ብንለው የተሻለ ይገልፀዋል ብዬ አስባለሁ። ኃጢያት በእግዚአብሄር ላይ የሚደረግ ወንጀል ነው። የዌስት ሚኒስተር ትንሹ ካቴኪዝም አስራ አራተኛ ጥያቄው ላይ 'ኃጢያት ምንድነው?' ብሎ ይጠይቅ ና ሲመልስ 'ኃጢያት የእግዚአብሄርን ሕግ አለመታዘዝ ወይም የእግዚአብሄርን ሕግ መተላለፍ ነው' ብሎ ያስቀምጠዋል።

በአጠቃላይ አዲስ ኪዳን ኃጢያትን ለመግለፅ 5 የተለያዩ የግሪክ ቃላትን ይጠቀማል፡

- ✓ *Hamartia*፡ አላማን መሳት ማለት ነው።

[25] The cross of Christ p.113

- ✓ *Adikia*፡ ፅድቅ አልባነትን ወይም ኢ-ሞራላዊነትን የሚያሳይ ነው።
- ✓ *Ponēria*፡ ክፋት ማለት ነው።
- ✓ *Parabasis (paraptōma)*፡ መተላለፍ ወይም ከተሰመረ ገደብ መውጣት ማለት ነው።
- ✓ *Anomia*፡ ህግን መተላለፍ ማለት ነው።

በእነዚህ በአምስቱም ቃላት ውስጥ የምንመለከተው ኃጢያት መደረግ የሌለበትን ማድረግ፤ መታለፍ የሌለበትን ማለፍ ነው። ኢሚል ብሩነር ስለ ኃጢያት ይህን ብለዋል፡ "ኃጢያት እንቢተኝነት፣ ትዕቢት፣ ከእግዚአብሄር ጋር እኩል ለመሆን መፈለግ ነው። ከእግዚአብሄር ጥገኝነት ለመላቀቅ የሚደረግ ሙከራ፤ በምክንያታዊነት፣ በምግባር ና በባህል ራስ-ገዝ ለመሆንም የሚደረግ ጥረት ነው።" ቶማስ ሽሬነርም "ኃጢያት መንፈሳዊ ግልሙትና ነው" ሲሉ አስቀምጠውታል። *በአጭሩ በውስጣችን ያለው በእግዚአብሄር ላይ የማመፅ ዝንባሌ ራስ ገዝ የመሆን ፍላጎት በተለያየ መጠን ሲገለጥ ኃጢያት ይባላል።*

## Mens Rea and Actus reus፡

ሰዎች የወደዱትን ለማድረግ ነፃ ፈቃድ አላቸው። ነፃ ፈቃድ ግን ሃላፊነትን ይዞ ይመጣል። ማለትም ሰዎች ለምርጫዎቻቸው ና ምርጫዎቻቸው ለሚያስከትሏቸው ውጤቶች ሃላፊነትን ይወስዳሉ። ከሃላፊነት ጋር አብሮ የሚመጣው ደግሞ ተጠያቂነት ነው። ፈቃድ፣ ሃላፊነት ና ተጠያቂነት በየትኛውም ውሳኔ ላይ ተከታትለው የሚመጡ ናቸው።

ሰዎች ኃጢያት ለመስራት ነፃ ፈቃድ አላቸው → ለሚሰሩት ኃጢያት ሃላፊነቱን ይወስዳሉ → ይህ ሃላፊነት ተጠያቂነትን ይዞ ይመጣል

ተጠያቂነት ኃጢያትን ከመስራት ና ለሰራነው ኃጢያት የሚኖርብንን ሃላፊነት ተከትሎ የሚመጣ ነው። ማለትም ሰው ተጠያቂ የሚሆነው ሃጢያት ስለ ሰራ ብቻ ሳይሆን ለሰራው ኃጢያት ሃላፊነት ስላለበትም ነው። ጳውሎስ በሮሜ መፅሀፍ የመጀመሪያ ሶስት ምዕራፎች ላይ የሚሞግተውም ይህን ነው። ከአህዛብ እንሻላለን የሚሉትን አይሁድ ህጉን ተላልፋችኋል ሲል እንደ አይሁዳውያኑ ህግ አልተሰጠንምና ተጠያቂ አይደለንም ይሉ የነበሩትን አህዛብ ደግሞ የሙሴ ህግ ባይኖራችሁም የህሊና ህግ ነበራችሁ ይላቸዋል። በእነዚህ ምዕራፋት ጳውሎስ የሚያደርገው ሁሉም ለሰራው ኃጢያት ሃላፊነት እንዳለበት ማለትም *የሚያመካኝው ነገር እንደሌለ* በማሳየት ሁሉም ተጠያቂነት እንዳለበት ማስረገጥ ነው። የኃጢያት ድርጊት መፈፀሙ ብቻ ሳይሆን ድርጊቱ ታስቦበት የተፈፀመ በመሆኑ ወንጀል ያደርገዋል። በተዘዋዋሪ የሰው ሃጢያት Actus reus (ድርጊታዊ) ብቻ ሳይሆን Mens Rea (ሃሳባዊ ፈቃድን) የሚይዝ ነው። በዚህም ወንጀል ነው። በስተመጨረሻም ተጠያቂነት ቅጣትን ይዞ የሚመጣ ነው።

ፈቃድ → ሃላፊነት → ተጠያቂነት → ቅጣት

# 2. የእግዚአብሄር ፃድቅ ፈራጅነት፡

እግዚአብሄር ፃድቅ ነው ስንል በእርሱ ዘንድ ኃጢያት የለም እያልን ብቻ ሳይሆን ኃጢያትን ሳይቀጣ የማያልፍ አምላክ ነው እያልን ነው። ፅድቅ ለእግዚአብሄር ባህርዩም ስጦታውም ነው። መፅሀፍ ቅዱሳችን የእግዚአብሄር ፅድቅ (dikaiōsynē theou) ብሎ ሲናገር በሁለት መንገዶች ያስቀምጠዋል። የመጀመሪያው በአማኞች ውስጥ ያለው የእርሱ ስጦታ የሆነው ፅድቅ ነው። ይህ ፅድቅ ደግሞ አማኞች በእምነት ብቻ ያገኙታል የተባለው ነው። (ሮሜ1፡17) ሁለተኛው ደግሞ የእራሱ የእግዚብሄር ባህርይ የሆነው ፅድቅ ነው። (ሮሜ3፡5፣26) ስለዚህ እግዚአብሄር ፃድቅ ነው ደግሞም አፅዳቂ ነው።

## እግዚአብሄር በኃጢያት ላይ ያለው ቁጣ ምን ይመስላል?

C.H. Dodd የተባሉ ፀሃፊ በሮሜ መፅሀፍ ማብራሪያ መፅሃፋቸው ላይ እንደሚናገሩት የእግዚአብሄር ቁጣ [orgē] ማለት የኃጢያት ተፈጥሮአዊ መዘዝ እንጂ የእግዚአብሄር በንቃት የሚሳተፍበት ስራው  አይደለም [It is impersonal and not active]። እንደ ዶድ ሃሳብ ኃጢያት የእግዚአብሄርን ንቁ ተሳትፎ የሚፈልግ ቁጣን የሚቀሰቅስ ሳይሆን ተፈጥሮአዊ መዘዝን [natural consequence] የሚያስከትል ብቻ ነው። ስለዚህ እግዚአብሄር ኃጢያትን ልቅጣ ብሎ አይቀጣም ይላሉ። እሳቸው እንደሚሉት ጳውሎስ ስለ እግዚአብሄር ፍቅር ሲያነሳ እግዚአብሄር ወደደን ይላል ነገርግን ስለ ቁጣው ሲያነሳ እግዚአብሄር ተቆጣን አይልም ስለዚህም ቁጣው እግዚአብሄር ሰዎች ላይ የሚፈፅመው ንቁ ተግባሩ [Has no personal sense] አይደለም።  ይህን የዶድ ሃሳብ አንዳንዶች ኢማነንቲስት (Immanentist) ምልከታ ብለው ይጠሩታል። እሳቸው ስለ ቁጣው ሲፅፉም፡

'[The wrath of God is]…not to describe the attitude of God to man, but to describe an inevitable process of cause and effect in a moral universe'[26]

ይህን ተፈጥሮአዊ መዘዝ ለማሳየት አንዳንዶች የሚጠቀሙት ምሳሌ፡ "አንድ ሰው በፍጥነት እያሽከረከረ ቢሄድ ትራፊክ ይዞ ሊቀጣው ይችላል (ይህ የህግ [legal] ቅጣት የምንለው ነው) ወይም ከአንዳች ነገር ጋር ሊጋጭ ይችላል (ይህ የኃጢያቱ መዘዝ [consequence] እንጂ የህግ ቅጣቱ አይደለም)። እነ ዶድ የኃጢያት ቁጣ መብራራት ያለበት በሁለተኛው ነው ይላሉ። እግዚአብሄር ኃጢያትን የሚቀጣ የተባለው ወይም የእግዚአብሄር ቁጣ የምንለው ልክ እንደ ትራፊኩ ህጋዊ በሆነ ገፀታ ሳይሆን የሰዎችን የኃጢያት መዘዝ ለማሳየት ብቻ ነው። ይህም የኃጢያት መዘዝ ሞት ነው።

ይህ ምልከታ በዶድ የሚታይ ብቻ ሳይሆን ሌሎች ምትካዊ ቅጣትን የማይቀበሉ ሰዎች ጋርም የሚታይ ነው። ከእነዚህ መካከል አንዱ ሶሲነስ ነው። ለምሳሌ፡ ሶሲነስ ፍትህ ና ምህረት የእግዚአብሄር ባህሪያት አይደሉም ይላል። ስለዚህ  እግዚአብሄር ፍትህንም ምህረትንም ለመስጠት በባህርይው አይገደድም።

---

[26] C.H. Dodd the Epistle of Paul to the Romans p. 23

ሁለቱንም መስጠት ወይም መከልከል ነፃ ፈቃዱ ነው ይላል። ለዚህ የሶሲነስ ሃሳብ መልስ የሰጡት ፍራንሲስ ቱረንቲን ሲሆኑ እሳቸው በዋነኛነት ያሳዩት በመጀመሪያ ሐጢያት ራሱ ህግን መተላለፍ መሆኑን ብሎም እግዚአብሄርም የአለም ዳኛ ‹ፈራጅ› መሆኑን ነው። ስለዚህ ስለ ኃጢያት ስናወራ አዲስ ኪዳን ከሚያስቀምጥበት የህግ አውድ ማውጣት የለብንም ብለው አስገንዝበዋል። እግዚአብሄር ዳኛ ነው ስንል በኃጢያት ላይ ይቆጣል ብሎም ይቀጣል እያልን ነው። ይህን የቱረንቲን ሃሳብ አር.ሲ ስፕሮል በመፅሀፋቸው በሠንጠረዥ አስቀምጠውት እናገኛለን[27]፡

| ኃጢያት | ሰው | እግዚአብሄር | ክርስቶስ |
|---|---|---|---|
| ዕዳ ነው ‹ማቴ 6፡12› | ባለዕዳ ነው | አበዳሪው ነው | ዋስ ነው ‹ዕብ7፡22› |
| ጠላትነት ነው ‹ሮሜ 8፡7› | ጠላት ነው | ተበዳይ ነው | አስታራቂ፤ መካከለኛ ነው ‹2ቆሮ5፡19› |
| ወንጀል ነው ‹1ዩሀ3፡4› | ወንጀለኛ ነው | ዳኛ ነው | ካህናችን ምትካችን ነው |

በቱረንቲን ና በፕሮቴስታንቱ መሠረት የእግዚአብሄር ፍርድ ተመጣጣኝ [retributive justice] ነው። ማለትም እግዚአብሄር ሳይቀጣው አደባብሶ የሚያልፈው ኃጢያት የለም። ይህን የእግዚአብሄር ፍትህ ይባላል። ብሉይ ኪዳን ላይ ይህ ፍርድ ደጋግሞ የታየ ሲሆን በአዲስ ኪዳንም የተለወጠ እግዚአብሄር አለ ካላልን በቀር የተለወጠ ነገር የለም። እግዚአብሄር በብሉይም በአዲስ ኪዳንም የተለወጠ ባህርይ የለውም። በብሉይ ሲቆጣ ሲፈርድ የምናውቀው እግዚአብሄር ራሱ የአዲስ ኪዳኑ እግዚአብሄር ነው። ቶማስ ሽሬነር በአዲስ ኪዳን የእግዚአብሄር ፍትህ ተመጣጣኝ መሆኑን የሚክዱትን ና ያለ ፍርድ እግዚአብሄር ኃጢያትን ይቀር ሊል ይችላል የሚሉትን ከማርሲዮን[28] ጋር ያነፃፅሯቸዋል፡

Indeed, those who think that the New Testament mutes the Old Testament emphasis on judgment have failed to read the New Testament carefully, for the New Testament regularly declares that a final judgment awaits those who forsake God and live disobedient lives. Modern-day Marcionism has by no means disappeared, but its kinder and gentler view of judgment can only be sustained by a more radical surgery than even Marcion attempted![29]

**እግዚአብሄር የሚፈልገው ምንድነው?**

እንደ እውነተኛ ዳኛ እግዚአብሄር የሚፈልገው ፍፁም የሆነን መታዘዝ ነው። የአቅማችንን ያህል እንድንሞክር ሳይሆን ህጉን ሙሉ በሙሉ አንድም ሳይቀር እንድንታዘዝ ይጠበቅብናል። በአንዱ ብንወድቅ ሕግን ሁሉ እንዳፈረስን ይቆጠራል። ***ሕግን ሁሉ የሚጠብቅ፥ ነገር ግን በአንዱ የሚሰናከል ማንም ቢኖር በሁሉ በደለኛ ይሆናል*** *‹ያዕ*2፡10› ይህም ማለት ለምሳሌ አንድ የሰው ነፍስ ያጠፋ

[27] The truth of the cross p.32
[28] ማርሲዮን [Marcion] በ2ኛው ምዕተ-አመት የነበረ የኑፋቄ አስተማሪ ሲሆን አንዱ ትምህርቱ የብሉይ ኪዳኑን እግዚአብሄር ከአዲስ ኪዳኑ መለየት ነበረ።
[29] The nature of the atonement four views

ወንጀለኛ በሕግ ፊት ቀርቦ “እስከዛሬ ሁሉን ሕግ ጠብቄያለሁ አትግደል የሚለውን ብቻ ዛሬ ጣስኩ ስለዚህ ልለቀቅ ይገባኛል” ማለት ይችላልን? ሕግን የጣሰ ሁሉ ወንጀለኛ የሚል ስም ይሰጠዋል ከዳኛውም የፍርድ ፅዋ ይጠጣል። እግዚአብሄር ደግሞ እውነተኛ ፃድቅ ዳኛ እንደመሆኑ ፍርዱ ተመጣጣኝ [retributive] ነው። የእግዚአብሄር ፍርድ ተመጣጣኝ ነው ስንል ሰሶስት ነገሮችን ያካትታል፡

- ✓ በደለኛው ላይ ይፈርዳል [guilty]፡ ዘፀ23፡7
- ✓ ለሁሉ ጥፋት ተመጣጣኝ ቅጣት ይሰጣል (ሁሉን እንደስራው ያስረክባል) [proportionality]፡ ሮሜ2፡6
- ✓ በሰዎች ፊት አድሎ አያደርግም [equity]፡ ሮሜ 2፡11

## Justice vs Violence

ብዙዎች የእግዚአብሄርን ቁጣ ሲያስቡ ከእግዚአብሄር ጥላቻ ወይም ቱግ ከሚል ስሜቱ የሚወጣ ነው እያልን ይመስላቸዋል ነገርግን የእግዚአብሄር ቁጣው ያለው ቅድስናው ጋር ነው። ፃድቅ ፈራጅ የሆነው ቅዱስ ስለሆነ ነው። የእግዚአብሄር ቁጣ እንደሰው ቁጣ አይደለም። ቅዱስ ነው!! ታዲያ የእግዚአብሄር ቁጣ ምንድነው? ብንባል መልሳችን፡

- ➢ የእግዚአብሄር ቁጣ እግዚአብሄር ለኃጢያት የሚያሳየው ቅዱስ ምላሽ ነው። ቅዱስ ነው ስንል ከኃጢያት ና ከእልኸኝነት የፀዳ እያልን ነው። እግዚአብሄር ቅዱስ እንደመሆኑ ኃጢያትን ይጠላል፤ ከኃጢያት ጋርም ህብረት የለውም። ኃጢያትን ማስተናገድ አይችልም። ለኃጢያት ያለው ምላሽም ቁጣው ነው። የእግዚአብሄር ቁጣ ራስን መቆጣጠር ካለመቻል የሚወጣ ግልፍተኝነትም አይደለም! ቅዱስ ነው!!! ሽሬነር በጥሩ ቃል ገልፀውታል፡ God does not become angry because he loses control of himself. His anger flows from his goodness, his matchless character. God’s anger does not call into question his goodness but is a manifestation of it: God’s goodness necessarily approves what accords with his character and repulses what stands contrary to it. So goodness necessarily loves what is right and hates what is evil. God’s wrath, then, is holy, righteous and unstained by any evil motive.[30]

እግዚአብሄር ኃጢያትን እንዴት ይመለከታል?:- እግዚአብሄር ለኃጢያት የሚያሳየውን ምላሽ በሚመለከት ጥሩ ገላጭ የሆነ ቃል የምናገኘው ኢየሱስ ለሎዶቅያ ቤተክርስቲያን በራዕይ 3፡16 ከተናገረው ላይ ነው። **እንዲሁ ለብ ስላልህ በራድም ወይም ትኩስ ስላልሆንህ ከአፌ ልተፋህ ነው።**

- ✓ *“ልተፋህ ነው”* ተብሎ የተተረጎመው የግሪክ ቃል *émeō’* የሚለው ሲሆን ቀጥተኛ ትርጉሙ ማስመለስ (ማስታወክ-- Vomit) የሚል ነው። እግዚአብሄር ለኃጢያት ያለው ምላሽ ይህ ነው

[30] Ibid

እንግዲህ!! እግዚአብሄር ኃጢያትን አደባብሶ ማለፍ ወይም አላምጦ መዋጥ አይችልም። ይህ ከቅዱስ ባህርይው ጋር አብሮ አይሄድም። እግዚአብሄር ኃጢያትን ይጠየፋል።

**እግዚአብሄር ና የእግዚአብሄር ምግባራዊ ህግ፡**

በተለምዶው ሰዎች ስለ እግዚአብሄር ምግባራዊ ህጎች ሲናገሩ ከምድራዊ ወይም ከተፈጥሮ ህጎች ጋር በምስስሎሽ ያቀርቡታል። ይህ በአጠቃላይ ተገቢ አይደለም ሊባል የሚችል ባይሆንም ነገርግን እጅግ አደገኛ አካሄድ ነው። የእግዚአብሄር ሞራላዊ (ምግባራዊ) ህጎች ከሌሎች ህጎች ጋር ብዙ ልዩነት አላቸው። ለምሳሌ፡ የኢትዮጵያ ህገ-መንግስት ከኢትዮጵያ መንግስት በላይ ነው። ማለትም የኢትዮጵያ መንግስት ራሱ ለህገ-መንግስቱ ተገዢ የመሆን ግዴታ ይኖርበታል።ወደ እግዚአብሄር ስንመጣ ግን ህጎች ከእግዚአብሄር በላይ አይደሉም። እግዚአብሄር የህጎቹ ሰጪ ና አስፈፃሚ እንጂ የህጎቹ እስረኛ ወይም ተገዢ አይደለም። 'ህጎቹ ምንድናቸው?' ካልን ታዲያ ህጎቹ የእግዚአብሄር ባህሪያት የተገለጠባቸው ናቸው። እግዚአብሄር ከህጎቹ የተፃረረ ነገር የማይሰራው በህጎቹ የሚገዛ ና የሚመራ ሆኖ ሳይሆን ህጎቹ የባህርይው ማሳያ ስለሆኑ ነው።

## Twofold nature in God

እግዚአብሄር የማይለያዩ ሁለትዮሽ ባህርያት አሉት። ፍቅር ነው፤ ቅዱስ ነው። ፀጋ ነው፤ እውነት ነው። አዳኝ ነው፤ ፈራጅ ነው። ቁጡ ነው፤ መሃሪ ነው። እነዚህ ባህሪያቱ እርስ በርሳቸው የሚጣሉ ሳይሆኑ አንዱ አንዱን ሳይለቅ አብረው የሚሄዱ ናቸው። በዚህ ውስጥ ትልቁ መሠረት እግዚአብሄር እንደማይለወጥ ማወቅ ነው። ማለትም ከእነዚህ ባህሪያቱ በተቃራኒ ሊሰራ አይችልም። ወይም ከሁለቱ ባህርያቱ አንዱን መርጦ ሌላውን ሊተው አይችልም። ፍቅርን መርጦ ፍርድን መተው አይችልም። ወይም አንዳንዶች እንደሚሉት ፍትሁን በፍቅሩ ውስጥ መገደብም አይችልም። እንደዛ ካደረገ በባህርይ መለወጥ ይደርስበታል፤ የሚለወጥ አምላክ ደግሞ በመሠረቱ አምላክም አይሆንም። ይህን ሁለትዮሽ ባህሪውን በሚገባ ካልተረዳን መስቀሉንም መረዳት አንችልም። ኤሚል ብሩነር በዚህ ላይ ሲናገሩ የዘመናዊ ሊበራል ሃሳቦች ምንጫቸው ይህን የእግዚአብሄር ሁለትዮሽ ባህርይ ሚዛናዊነት መሳት ነው ይላሉ፡

'..due to the fact that the idea of the Divine Holiness has been swallowed up in that of the Divine love; this means that the biblical idea of God, in which the decisive element is this twofold nature of holiness and love, is being replaced by the modern, unilateral, monistic idea of God'—Emil Brunner in The Mediator

በዚህ ሁለትዮሽ ባህሪው ውስጥ ታዲያ እግዚአብሄር ማድረግ ባለበት (what he ought to do) ና በሚያደርገው (what he will do) መካከል አጣብቂኝ (dilemma) እንዲፈጠር ያደርጋል። ለምሳሌ፡

- እግዚአብሄር ቅዱስ ነውና ኃጢያተኛን መቅጣት አለበት ነገርግን ፍቅር ነውና ኃጢያተኛን ለማዳን ይወዳል!! ቅድስናውን ላለመተው መቅጣት ቢኖርበትም ነገርግን እንዳያጠፋን እጅግ ይወደናል። ታዲያ እንዴት ቅድስናውን ና ፃድቅ ፈራጅነቱን ሳይተው ያድነን?

ይህን በደንብ ለመረዳት በመፅሀፍ ቅዱስ በተመሳሳይ አጣብቂኝ ውስጥ የነበረ አንድ ንጉስ አንስተን እንይ። በዳንኤል 6 ላይ የምናገኘው ንጉስ ዳርዮስ በመንግስቱ ላይ 120 መሳፍንትን ና ከዳንኤል ጋር ደግሞ 3 መሪዎችን በምድሩ ላይ ይሾማል። በኋላ በዳንኤል ጥበብ የተማረከው ንጉስ በመላው መንግሰቱ ላይ ሊሾመው መነሳቱን ያዩ የዳንኤል የስራ ባልደረቦች ዳንኤል ላይ መሸረብ ይጀምራሉ። ነገርግን ከዳንኤል የፀሎት ህይወት በቀር አንዳች ነቀፌታ አላገኙበትም። ወደ ንጉሱም ሄደው በግዛቱ ለ30 ቀን የትኛውም ሰው ወደ ንጉሱ ካልሆነ በቀር ወደ ሌላ አምላክ እንዳይፀልይ አዋጅ እንዲያወጣ አዋጁንም የተላለፈ ወደ አንበሳ ጉድጓድ እንዲጣል ፍርድ እንዲያስተላልፍ ያግባቡታል። ንጉስ ዳርዮስ በዚህ ተደስቶ ህጉን በማይሻር የፋርስ ና ሜዶን ቀለበት አትሞ አወጀው። ዳንኤል ግን ፀሎት ከሚያቆም እስትንፋሱ ቢቆም እንደሚመርጥ አሳየ። በፊት ከሚያደርገው አንዳች የፀሎት ጊዜ ሳያጓድል ፀሎቱን ቀጠለ። በኋላም ከሳሾቹ በእርሱ ላይ ያሰቡትን ለመፈፀም የተሳካላቸው መሆኑን አይተው ወደ ንጉሱ በመሄድ ዳንኤል አዋጁን እንዳላከበረ ለንጉሱ አረዱት። ይህን በሰማ ጊዜ የንጉሱ ምላሽ ይህ ነበረ፡

***ንጉሡም ይህን ቃል በሰማ ጊዜ በጣም አዘነ፥ ያድነውም ዘንድ ልቡን ወደ ዳንኤል አደረገ ሊያድነውም ፀሐይ እስኪገባ ድረስ ደከመ። ዳን 6፡14***

ንጉሱ የገባበት አጣብቂኝ ይህ ነው፡

1. ለዳንኤል ፍቅር ስላለው እንዲሞት አሳልፎ መስጠት አልፈለገም፤
2. ላወጣው ትዕዛዝ ግዴታ መገዛት ስላለበት ዳንኤልን አሳልፎ መስጠት አለበት።

ንጉሱ ምን አደረገ? <u>ከፍቅሩ ይልቅ ፍርዱን መረጠ!!</u> ዳንኤልን አሳልፎ ሰጠው። ማዳን ቢፈልግም ማዳን አልቻለም።

ይህን ታሪክ ያነሳሁት ከእኛ መዳን ጋር ቀጥታ የሚገናኝ ስለሆነ ሳይሆን በፍቅር ና በፍርድ መካከል አጣብቂኝ ውስጥ መግባት ምን ያህል ከባድ እንሆነ ለማሳየት ነው። እግዚአብሄር እንዲሁ፡

- እግዚአብሄር ቅዱስ ነው ስለዚህ ኃጢያተኛን መቅጣት አለበት
- እግዚአብሄር ሰዎችን ይወዳል ስለዚህ ማዳን ይፈልጋል

ንጉስ ዳርዮስ ፍርዱን መርጠ! እግዚአብሄር ግን ፍርዱን መርጦ ፍቅሩን ይተው ዘንድ ሰው አይደለም። ይልቁንስ ወልድ ስጋ ሆኖ ወደ ታች ወረደ። የኃጢያተኛውን ቅጣት ተቀበለ ስለ እኛ ተሰቃየ ደቀቀ!! እኛም ድነትን አገኘን!! ክርስቶስ በእኛ ቦታ ሆኖ ቅጣታችንን ተቀብሎልናልና። ይህን ነው እንግዲህ የቅጣት ምትክነት ቤዝሆት ብለን የምንጠራው። ክርስቶስ ስለ እኛ ሞቶ አዳነን።

ታዲያ እኛ ክርስቲያኖች 'ክርስቶስ ማነው?' ስንባል እንዲህ እንላለን፡

- ክርስቶስ የእግዚአብሄር ፍቅር ና ፍትህ የተገለጡበት የእግዚአብሄር ጥበብ ነው። በክርስቶስ የእግዚአብሄር ፍትህም ፍቅርም ተሟልቷል። እግዚአብሄር አለምን ከፈጠረበት ጥበቡ ይልቅ ፍቅርን ና ፍትህን በመስቀሉ ያስታረቀበት ጥበቡ ምነኛ ድንቅ ነው… በክርስቶስ ***ምሕረትና***

***እውነት ተገናኙ ጽድቅና ሰላም ተስማሙ*** (*መዝ* 85፡10) እንላለን። እግዚአብሄር ፅድቁን ሳይተው ያፀደቀን በእርሱ ነው፡ ***ራሱም ጻድቅ እንዲሆን በኢየሱስም የሚያምነውን እንዲያጸድቅ*** ..(*ሮሜ*3፡26)

# ኃጢያት፣ የእግዚአብሄር ፍትህ ና የቤዝሆት ቲዎሪዎች፡

የተለያዩ የቤዝሆት ቲዎሪዎች ለመኖራቸው ምክንያቱ በቤተክርስቲያን ታሪክ ውስጥ ስለ ኃጢያት ያለው ምልከታ የተለያየ መሆኑ ነው። ፔላጂያን፣ ገሚስ ፔላጂያን ና አውግስቲኒያን ያላቸው የኃጢያት ምልከታ የተለያየ እንደመሆኑ ማዕከላዊ አድርገው የሚጠቀሙበት የቤዝሆት ቲዎሪም የተለያየ ነው። ይህንንም ሉዊስ በርኮፍ በጥሩ መልኩ አስቀምጠውታል፡

Just as a doctor's diagnosis of a disease determines what medicines he will prescribe to check and counteract its ravages, so a theologian's conception of sin will have a determining influence on his view of the redemptive work of God in Christ.[31]

ለአንድ በሽታ የሚኖረን የምርመራ ውጤት የህክምናችንን አቀራረብ እንደሚወስን ሁሉ ስለ ኃጢያት ያለን አመለካከት ስለ ቤዝሆት ያለንን ማዕከላዊ ቲዎሪ ይወስናል። የተበላሸ የኃጢያት ምልከታ ያለው ሰው በፍፁም የተስተካከለ የቤዝሆት ቲዎሪ ሊኖረው አይችልም። ለኃጢያት ቀለል ያለ አመለካከት ያላቸው ሰዎች በፍፁም የምትካዊ ቅጣት ቤዝሆትን ሊቀበሉ አይችሉም። የምትካዊ ቅጣት ቤዝሆት ቲዎሪን ለመቀበል በዚህ ምዕራፍ እንዳየነው ሁለትን ነገሮችን በሚገባ መረዳት ያስፈልገናል፡

1. የኃጢያትን አስከፊነት
2. ኃጢያት በእግዚአብሄር ፊት የሚቀሰቅሰውን ቁጣ

ይህ ዘመን ለምን ይሆን የምትካዊ ቅጣት ቲዎሪን እየገፋ ያለው የሚለውን ብናይ እንኳን ዘመናችን ለኃጢያት ያለው ምልከታ በጣም የወረደ መሆኑን አንዱ ምክንያት ነው። ይህን ቲዎሪ እንደ ጉድ ከሚጠሉት መካከል የሆኑትን ሊበራሎችን ማየት ደግሞ ለዚህ በቂ ነው። ኃጢያትን የሚንቅ የሚዳፈር ትውልድ ትክክለኛ የቤዝሆት ምልከታ እንዲኖረው መጠበቅ ዘበት ነው። ስለ ገዛ ኃጢያቱ ራሱ የማይቆጣ ትውልድ ኃጢያቱ በእግዚአብሄር ፊት ሊያመጣ የሚችለውን ቁጣ መረዳት አይችልም። በዚህ ረገድ አር.ደብሊው. ዴል ጥሩ ሃሳብ አስቀምጠውልናል፡ “it is partly because sin does not provoke our own wrath, that we do not believe that sin provokes the wrath of God”.—R.W. Dale

[31] Vicarious atonement p.20

# ክፍል-3

# ምትካዊ ቅጣት ቤዝሆት በመፅሀፍ ቅዱስ ያለው ቦታ:

# IS IT BIBLICAL?

በመፅሀፍ ቅዱስ ውስጥ ቤዝሆት ተያይዞ የተቀመጠው ከመስዋዕት ጋር ነው። (ማር14፡24፣ ሮሜ5፡6፣ ገላ2፡21...) በሚቀጥሉት ገፆች እንደምናየው በብሉይ ኪዳን ውስጥ ለሃጢያት ስርየት የሚቀርቡ መስዋዕቶች ሁለት አይነት ጥቅም ነበራቸው፡

1. ለህዝቡ የኃጢያት ስርየት ያመጣሉ ፡
2. የእግዚአብሄርን ቁጣ ያስታግሳሉ፤ የእግዚአብሄርን ፍትህ ያረካሉ።

ክርስቶስ የኃጢያት መስዋዕት መሆኑን ከተቀበልን (ሮሜ8፡2) በእርሱ ሞት የኃጢያት ስርየት ማግኘታችንን ብሎም ከእግዚአብሄር ቁጣ መዳናችንን መቀበል ግድ ይለናል። እርሱ ኃጢያታችንን ተሸክሟል፤ የእግዚአብሄር ቁጣም በመስቀል ላይ አርፎበታል። ከዚህ ውጪ ፅድቅ ሊኖረንም አይችልም።

# ክርስቶስ ስለ እኛ እርግማን ሆነ? ‹ገላ3፡13›

### ***በእንጨት የሚሰቀል ሁሉ የተረገመ ነው ተብሎ ተጽፎአልና ክርስቶስ ስለ እኛ እርግማን ሆኖ ከሕግ እርግማን ዋጀን፤*** (ገላ3፡13)

ይህን ክፍል ለመረዳት ‘እርግማን’ በራሱ ምንድነው? የሚለውን መመለከት አስፈላጊ ነው። እግዚአብሄር ከእስራኤል ጋር ኪዳን ሲገባ ና ሕጉን ሲሰጣቸው ቅድመ ሁኔታዎችን አካቶ ነበረ። ልክ በእኛ ዘመን ውል በሚገቡ ሰዎች መካከል ውሉን ከመጠበቅ ጋር የሚመጣ ሽልማት ውሉን ከማፍረስ ጋር ደግሞ የሚመጣ ቅጣት እንዳለ ሁሉ ለአይሁድ ከሕጉ ጋር የተያያዘ በረከት እና እርግማን አለ። በረከቱ ሕጉን በአግባቡ ለሚጠብቁት ሲሆን እርግማኑ ደግሞ ሕጉን ለተላለፉት ነው። ይህንንም በዘዳግም 28፡ 2 ፣ 15 ላይ በንፅፅር መመልከት ይቻላል።

ታዲያ በረከቱ ምንደነው? እርግማኑስ ምንድነው?

በረከት ተብለው የተዘረዘሩትን ሁሉ በአንድ ሃሳብ እንጠቅልል ቢባል ዘኁልቁ 6፡24-26 ወደ ተፃፈው መሄድ በቂ ሊሆን ይችላል። በረከቱ የተገለፀው ከእግዚአብሄር አብሮነት ጋር ነው። እስራኤል ለኪዳኗ ታምና ሕጉን ከታዘዘች እግዚአብሄር አብሯት ይሆናል። ፊቱን ያበራላታል። ትልቁ የእስራኤል በረከት እግዚአብሄርን ማየት ነው። በዚህ መሠረት እርግማን ምንድነው? የሚለው በራሱ ግልፅ ይሆናል። እርግማን ከእግዚአብሄር መራቅ ነው። ከእግዚአብሄር መለየት ነው። ከእግዚአብሄር መለየት ደግሞ መንፈሳዊውን ሞት መሞት

ነው። ጌታችን እንግዲህ እርግማን ሆነ ብሎ ሐዋሪያው ሲነግረን በዛ ቅፅበት ውስጥ ከእግዚአብሄር ተለይቶ እንደነበረ እያስቀመጠ መሆኑ ግልፅ ነው። ጌታችንም በመስቀል ላይ እንዲህ ብሏልና፡ **አምላኬ አምላኬ፥ ስለ ምን ተውኸኝ?** ‹**ማቴ**27፡46›

እንግዲህ እግዚአብሄር ክርስቶስን መስቀል ላይ አልተወውም ካልን ለኃጢያታችን ተገቢው ዋጋ አልተከፈለም እያልን ነው። ምክንያቱም ክርስቶስ እርግማን ሆኖ እኛን ከእርግማን ካልዋጀን እነሆ በእርግማናችን ውስጥ እስካሁን አለን። ጆን ኦውን “If he fulfilled not justice, I must; if he underwent not wrath, I must to eternity” ብለው መናገራቸውም ለዚህ ነው። ‹ገላ3፡13› መሠረት መዳናችን የተመሠረተው በዚህ የክርስቶስ ስራ ላይ ነው፤ በመስቀል ላይ ክርስቶስ እርግማናችንን ማለትም የሕግ መተላለፋችንን ሁሉ ተሸክሟል። ለኃጢያታችንም መከፈል የነበረበት እዳ ሁሉ ተከፍሏል።

# ዘፀአት 12፡

የዘፀዐት መፅሀፍን ስናጠና የእስራኤልን ከግብፅ መዳን ብቻ የምናይ ከሆነ ግማሽ እውነት ብቻ ይሆንብናል። እውነት ነው እግዚአብሄር በግብፅ ምድር ሃይሉን ገልጦ የግብፅን አማልክት አንበርክኮ ዘርሮ ህዝቡ ከጠላት ሰፈር አውጥቷል። ይህ ግን ግማሽ እውነት ብቻ ነው። የቀረው ግማሹ ምንድነው ካልን ኦሪት ዘፀዐት ምዕራፍ 12 እንዲህ ይነግረናል፡

***ደሙንም ባየሁ ጊዜ ከእናንተ አልፋለሁ እኔም የግብፅን አገር በመታሁ ጊዜ መቅሰፍቱ ለጥፋት አይመጣባችሁም።*** (ቁ.13)

ኦሪት ዘፀዐት እስራኤል ከግብፅ እንደዳነች ብቻ ሳይሆን ከእግዚአብሄርም ፍርድ የዳነችበት ታሪክ የሚግረን መፅሀፍ ነው። **ከግብፅ በእግዚአብሄር ሃይል ስትድን ከእግዚአብሄር ፍርድ ደግሞ በበጉ ደም ድናለች።**እውነት ነው ቁጣው ያነጣጠረው የግብፅ አማልክት ላይ ነው። ነገርግን የግብፅን አማልክት እስራኤልም ከግብፃውያኑ ባልተናነሰ ስታመልክ ቆይታለች። (ህዝ 20፡4-10) በዚህም ምክንያት ከግብፅ እኩል የሚያጠፋትን ኃጢያት ተሸክማለች። ከክፍሉም እንደምናየው **የግብፅን በኩር ለመምታት የመጣው ፍርድ በግብፃውያን ና በእስራኤላውያን መካከል ያገኘው ልዩነት የዘር ወይም የቅድስና ልዩነት ሳይሆን የበጉ ደም ነው።** የበጉን ደም ያላደረገ እስራኤላዊ ቢኖር ከቁጣው የሚያመልጥበት አንዳች መንገድ አልነበረውም። እስራኤላውያን ከቁጣው በምን አመለጡ? በእነርሱ ቦታ በሞተው በግ ደም! በጉ የታረደው በምትክነት ነው። እነርሱ ሊቀበሉ የሚገባቸውን የኃጢያት ቅጣት (ሞት) በጉ ተቀበለ።

በክርስቶስም ያገኘነው ተመሣሣይ ነገር ነው፡ ክርስቶስ ከኃጢያት፣ ከአለም፣ ከሰይጣን ባርነት ነፃ አውጥቶናል። ነገርግን ይህ ግማሹ እውነት ነው.. ክርስቶስ ከእግዚአብሄርም ቁጣ አድኖናል። እንዴት? ቁጣውን እርሱ ተቀብሎ። የኃጢያታችንን ቅጣት እርሱም ሞትን ተቀብሎ። ለዚህም ነው መፅሀፍ ቅዱስ በፋሲካው በግ ና በክርስቶስ መካከል ብዙ ምስስሎሽ የሚሰራው፡ ዩሀ19፡35-36፤ ዘፀ12፡46 ፣ 1ጴጥ1፡18-19 ፣ 1ቆሮ5፡7…

# ዘሌዋውያን፡

የዘሌዋውያን መፅሀፍ ዋነኛ መልዕክት 'ቅዱሱ እግዚአብሄር በሃጢያተኛው ህዝብ መካከል እንዴት ሊገኝ ይችላል?' የሚለው ነው፡፡ ይህ ለእስራኤል አደገኛ ነበረ፡፡ ምክንያቱም ቅዱሱ እግዚአብሄር ኃጢያትን ሳይቀጣ አያልፍምና ለኃጢያታቸው መፍትሄ ካልተፈለገ በመካከላቸው ሲያድር ፍርዱን ማሳየቱ አይቀሬ ይሆናል፡፡ ስለዚህ የዘሌዋውያን መፅሀፍ ለዚህ መፍትሄ ያበጃል፡፡ መፍትሄውም ተገቢ መስዋዕት ማቅረብ ነው፡፡ የመስዋዕት ስርዐቱን በሚገባ ማጥናት ለርዕሰ-ጉዳያችን እጅግ አስፈላጊ ነው፡፡ ምክንያቱም በአዲስ ኪዳን የክርስቶስ ሞት ተያይዞ የሚጠቀሰው ከብሉይ ኪዳን መስዋዕት መቅረብ ጋር ነው፡፡ ለምሳሌ፡ ኤፌ 5፡2፤ ሮሜ 3፡25፣ 8፡3 ፤ ዕብ 9-10 ፣ .. ወዘተ ማንሳት እንችላለን፡፡

በአጠቃላይ ከተመለከትነው የብሉይ ኪዳን መስዋዕቶችን በሁለት መክፈል እንችላለን፡

- ✓ የመጀመሪያው ከእግዚአብሄር ጋር ለመገናኘት (ህብረት ለማድረግ) የሚቀርቡ ለምሳሌ፡ የህብረት መስዋዕት፣ የሚቃጠል መስዋዕት..
- ✓ ሁለተኛው ደግሞ ለኃጢያት የሚቀርቡ ለምሳሌ፡ የኃጢያት መስዋዕት፣ የበደል መስዋዕት

ዘሌዋውያን መፅሀፍ በአጠቃላይ 5 አይነት የመስዋዕት አይነቶችን ሲያስቀምጥ ከእነርሱ መካከል ከእህል-ቁርባን ውጭ ያሉት አራቱ የደም መስዋዕቶች ናቸው፡፡ ሌዎን ሞሪስ በዚህ ላይ ጥሩ ማጠቃለያ ሠንጠረዥ አዘጋጅተውልናል[32]፡

**THE ANIMAL SACRIFICES IN LEVITICUS**
(figures refer to chapter and verse in Leviticus)

| | Burnt | Peace | Sin | Guilt |
|---|---|---|---|---|
| 1. The worshipper 'brings near' | male from flock or herd: bull, sheep or goat; dove or pigeon (1:5, 10, 14) | domestic animal, male or female (3:1, 6, 12) | for priest or people, young bull (4:3, 13f.); for leader, male goat (4:22f.); for citizen, female goat (4:27f.) or lamb (4:32) | ram plus silver (5:15) |
| 2. The worshipper lays his hand on the head of the prescribed victim | | | | |
| 3. The worshipper himself kills the prescribed victim | | | | |
| 4. The priest puts the blood | against the altar on all sides (1:5,11); drains blood of birds on side of altar (1:15) | against the altar on all sides (3:2, 8) | for priest or the community, seven times before the curtain, on horns of incense altar, at base of main altar (4:6f., 17f.); for individual, on horns and at base of main altar (4:25, 30) | against the altar on all sides (7:2) |
| 5. The priest burns on the altar | the whole animal or bird (1:9, 13, 17) | specified parts (3:3f., 9f., 14f.) | as for peace offerings (4:8–10) | specified parts (7:3f.) |
| 6. Disposal of the rest of the carcase | — (the hide to the priest, 7:8) | parts to the priest (7:31–34); the rest eaten by worshippers (7:15–21) | for priest or community, burnt outside the camp (4:11f., 21); for individuals, eaten by priestly males (6:25f., 29) | eaten by priestly males (7:6) |

[32] The Atonement Its Meaning and Significance by Leon L. Morris

በዘሌዋውያን መፅሀፍ መስዋዕት የህዝቡን ኃጢያት ማስወገድ ብቻ ሳይሆን የእግዚአብሄርን ቁጣ ማስታገስም የሚችል ነው። ይህን ለማሳየት ሁለት ክፍሎችን፡ ዘሌዋውያን 9:24 ና 10:2 ን እናስተያይ፡

**እሳትም ከእግዚአብሔር ዘንድ ወጣ፥ በመሠዊያውም ላይ የሚቃጠለውን መሥዋዕት ስቡንም በላ ሕዝቡም ሁሉ አይተው እልል አሉ፥ በግምባራቸውም ወደቁ።** (ዘሌ9፡24)

**እሳትም ከእግዚአብሔር ፊት ወጥቶ በላቸው፥ በእግዚአብሔርም ፊት ሞቱ፡፡** (ዘሌ10፡2)

በምዕራፍ 9 ላይ አሮን ከእግዚአብሄር የተሰጠውን ትዕዛዝ በአግባቡ በመከተል መስዋዕቱን ሲያቀርብ እንመለከታለን። በውጤቱም የእግዚአብሄርም እሳት ከሰማይ ወርዳ መስዋዕቱን በላች። ከአንድ ቁጥር በኋላ በምዕራፍ 10 ላይ የአሮን ልጆች ባልታዘዙት መንገድ መስዋዕቱን አቀረቡ። በውጤቱም የእግዚአብሄር እሳት ከሰማይ ወርዳ በላቻቸው። **በሁለቱ ታሪኮች መካከል ያለው ምስስሎሽ፡ በሁለቱም ላይ የእግዚአብሄር እሳት ከሰማይ መውረዷ ሲሆን ልዩነቱ ግን ወርዳ የበላችው ነገር ላይ ነው።** በመጀመሪያው መስዋዕቱን በላች በሁለተኛው ሰዎቹን በላች!! ከዚህ የምናየው የእግዚአብሄር ቁጣ ኃጢያት ላይ መፍሰሱ አይቀሬ ነው። ጥያቄው ማን ላይ ነው የሚፈሰው የሚለው ብቻ ነው። መስዋዕቱ ላይ ወይስ ኃጢያተኛው ላይ? ከዚህ እንደምናየው መስዋዕት አላማው የእግዚአብሄርን ቁጣ ማብረድም ጭምር እንደሆነ ግልፅ ነው። ክርስቶስ ስለ እኛ የኃጢያት መስዋዕት ሆኖ ሲቀርብ በእኛ ላይ መውረድ የነበረበትን የእግዚአብሄር ቁጣ እርሱ ተቀብሎልን ነው። መስዋዕቱ ላይ የወረደ የእግዚአብሄር ቁጣ የለም ካልን እንግዲያውስ እኛን የሚጠብቀን ቁጣ አለ እያልን ነው።

## የስርየት ቀን [Yom kippur] --ዘሌዋውያን 16

የስርየት ቀን ለአይሁዳውያን በአመት አንድ ጊዜ የሚከወን ስርዐት ሲሆን ሊቀካህናቱ ለህዝቡ ና ለራሱ ኃጢያት መስዋዕትን ይዞ ወደ መገናኛው ድንኳን ወደ ቅድስተ-ቅዱሳን የሚገባበት ጊዜ ነው። በዘሌዋውያን መፅሀፍ ምዕራፍ 16 ላይ በምናገኘው ክፍል አሮን በታላቁ የስርየት ቀን ላይ ሁለት ፍየሎችን ለኃጢያት መስዋዕት እንዲያዘጋጅ ተነግሮታል። የመጀመሪያው ፍየል መገናኛው ድንኳን በረከሱ ሰዎች መካከል በመገኘቱ ለመገናኛው ድንኳን ስርየት የሚደረግ ሲሆን ሁለተኛው ፍየል ግን ለህዝቡ ኃጢያት ወደ ምድረ-በዳ የሚለቀቅ [scapegoat] ነው። በመጀመሪያ አሮን በሁለተኛው ፍየል ራስ ላይ እጁን በመጫን የህዝቡን መተላለፍ ሁሉ ይናዘዛል። እጅ መጫን የሚናረው ስለ ምትክነት ነው፤ ከመስዋዕቱ ጋር መቆጠርን የሚያሳይ ነው። በዚህ መሠረት የህዝቡ ኃጢያት ሁሉ በፍየሉ ላይ እንዳለ ይቆጠራል። (ቁ. 22) ከዚያም ፍየሉ ወደ ምድረ-በዳ ይለቀቃል።

የፍየሉ ወደ ምድረ-በዳ መለቀቁ ምንን ያሳያል?

- ✓ ይህ በቀጥታ የሚጠቁመን የእግዚአብሄርን ፍርድ ወይም ቁጣ ነው። ወደ ምድረ-በዳ መለቀቅ የሚለው ከህዝቡ መለየትን የሚያሳይ ሲሆን ከህዝብ መለየት ደግሞ በዘሌዋውያን መፅሀፍ ውስጥ በተደጋጋሚ የእግዚአብሄርን ፍርድ ሲያመለክት ይታያል። (ዘሌ7፡20፤ 18፡29፤ 22፡3…)

ስለዚህ በምትክነት የቀረበው ፍየል የህዝቡን የኃጢያት ጥፋተኝነት ብቻ ሳይሆን ቅጣትም እንደተሸከመ እንደመለከታለን።

- ✓ ይህን ለመደገፍ ሌላው ማስረጃ በቁጥር 22 ላይ የሚገኘው የዕብራይስጥ ሃረግ ነው። *'nasa awon'* የሚለው ሃረግ ሐጢያትን መሸከም ተብሎ ተተርጉሟል። ሐጢያትን መሸከም በሚለው ውስጥ ግን የሐጢያትን ጥፋተኝነት ብቻ ሳይሆን የሐጢያትን ቅጣት መሸከምን እንደሚያመለክት ለመገንዘብ ቃሉ አገልግሎት ላይ የዋለባቸውን ሌሎች ክፍሎች መመልከት አስፈላጊ ነው። ለምሳሌ፡ ዘፍ4፡13፣ ዘሌ5፡17 ፣ ዘኍ5፡31… በእነዚህ ክፍሎች ሐጢያትን መሸከም ምትክነት ብቻ ሳይሆን ቅጣትንም መሸከም እንደሚያመለክት ማየት እንችላለን።

በዘሌዋውያን ውስጥ የምናገኘውን ለኃጢያት ስርየት የሚሆን የእንስሳት መስዋዕት በሚመለከት የዕብራውያን ፀሀፊ ሲናገር "***የኮርማዎችና የፍየሎች ደም ኃጢአትን እንዲያስወግድ የማይቻል ነውና***" (***ዕብ***10፡4) ይላል። ለሰው ሃጢያት እንስሳ መቅረቡ የሚያረካ ምትክነት [satisfactory substitute] አይደለም። ይልቁንስ ለሰው ሐጢያት ምትክ የሚሆነው ንፁህ ሰው ነው። በዚሁ ስለዚህ ንፁህ መስዋዕት ትንቢት ወደ ተነገረበት ወደ ኢሳይያስ መፅሀፍ እናልፋለን።

# ትንቢት- ኢሳይያስ፡

በቅጣት ምትክነት አስተምሮ ውስጥ ትልቅ ቦታ የሚሰጠው የመፅሀፍ ቅዱስ ክፍል የኢሳይያስ መፅሃፍ 53ኛው ምዕራፍ ነው። በዚህ ክፍል ውስጥ መጀመሪያ መመለስ ያለብን ኢሳይያስ የሚናገረው ስለ ክርስቶስ ነው ወይ? የሚለውን ነው። ይህ ክፍል በአዲስ ኪዳን ተደጋግመው ከተጠቀሱ የመፅሀፍ ቅዱስ ክፍሎች ውስጥ የሚገኝ ሲሆን በዚህ ምዕራፍ ውስጥ ከሚገኙ 12 ቁጥሮች ውስጥ 10 የሚሆኑት በአዲስ ኪዳን ተጠቅሰው እናገኛለን። ምዕረፉ በተጠቀሰባቸው አውዶች ሁሉ ስለ ክርስቶስ ሞት ማስረጃ ሆኖ ቀርቧል። ምናልባት ከዚህ ትንሽ የሚለይ የሚመስለው የማቴዎስ ወንጌል ምዕራፍ 8 ቁጥር 17 ላይ የተጠቀሰበት መንገድ ነው። ማቴዎስ "**ደዌያችንን ተቀበለ፤ ሕመማችንን ተሸከመ**" የሚለውን ከኢሳ 53 ወስዶ ከክርስቶስ ሞት ጋር ሳይሆን ከክርስቶስ የፈውስ አገልግሎት ጋር ያገናኘው ይመስላል። ነገርግን በዚህ ላይም ቢሆን ማቴዎስ ክፍሉን ኢሳይያስ ላይ ከተናገረበት የሚሰቃይ መሲህ አውድ ገንጥሎ እንዳልተጠቀመው እውቁ ስኮላር ዲ.ኤ ካርሰን ሲሞግቱ እንዲህ ይላሉ፡

> But strictly speaking Isaiah 53:4 simply speaks of the Servant's bearing infirmities and carrying sicknesses; and it is only the context, plus the connection between sickness and sin, that shows that the way he bears the sickness of others is through his suffering and death... This means that for Matthew, Jesus' healing miracles pointed beyond them selves to the Cross. In this he is like the evangelist John, whose "signs" similarly point beyond themselves.[33]

[33] D.A. Carson commentary on Matthew (The EXPOSITORS BIBLE COMMENfARY vol.8)

ስለዚህ በካርሰን ሃሳብ መሠረት ማቴዎስ የኢሳይያስ 53ን ክፍልን ከመንፈሳዊ ትርጉሙ ማለትም ከኃጢያት ነጥሎ እየተጠቀመበት ሳይሆን በመንፈሳዊው ና በስጋዊው መካከል ያለውን ግንኙነት ያስቀመጠበት ነው። ስጋዊው በሽታ ምንጩ መንፈሳዊው ኃጢያት ስለሆነ ክርስቶስ ኃጢያታችንን ሲሸከም ይህንን በሽታም ሊያስወግድ መሆኑ ግልጥ ነው። ይህም ዳግም በመምጣቱ ዕውን የሚሆን እውነት ነው። በዚህ መሠረት ማቴዎስ በሚያስገርም መልኩ የክርስቶስን የፈውስ አገልግሎት ከመስቀሉ ጋር አገናኝቶ ያስቀመጠበት እንጂ ኢሳ53ን ከመስቀሉ አውድ ገንጥሎ እያወጣው አለመሆኑን ማየት ይቻላል።

ኢሳ 53 ከሌሎች የብሉይ ኪዳን ክፍሎች በተለየ መልኩ አንድ ሰው ለሌላው ኃጢያት ሲሸከም፤ እንዲሁም ሲቀጣ የሚያሳይ ነው። ሌሎች የብሉይ ኪዳን ክፍሎች በሰዎች ቦታ በጎች፣ ፍየሎች፣ ኮርማዎች ና ሌሎች እንስሳት መስዋዕት ሲሆኑ እንጂ አንድ ሰው የሌላውን ኃጢያት ተሸክሞ መስዋዕት ሲሆን አይታይም። ይህ ግን በኢሳይያስ መፅሃፍ ሲቀየር እንመለከታለን።

ኢሳይያስ 53 ስለ መሲሁ የሚናገር መሆኑ ግልፅ ከሆነ የክፍሉን ሃሳብ ስንመረምር ስለ ክርስቶስ ሞት ብዙ ነገሮችን እንድንገነዘብ ይረዳናል። ከእነዚህም መካከል ክፍሉ የሚከተሉትን ያንፀባርቃል፡

1. የክርስቶስ ምትክነት በግልጥ የተቀመጠበት ነው። (53፡5)
2. የክርስቶስ ሞት የኃጢያት መስዋዕትነት ነው። (53፡10)
3. ክርስቶስ የማዳኑን ግብር የፈፀመው በፈቃዱ ብቻ ነው። (53፡4)
4. የክርስቶስ ሞት የአብ ፈቃድ ነበረ። (53፡10)-- በዚህ ላይ በተጨማሪ ዘካ13፡7 (ማር 14፡27) እረኛውን የመታው እግዚአብሄር ለመሆኑን በግልጥ ያስተምሩናል።
5. ክርስቶስ ከኃጢያት ንፁህ ነበረ። (53፡9)
6. ክርስቶስ የኃጢያተኞችን በደል ተሸከመ። (53፡6፣12)
7. ይህ የእግዚአብሄር የማዳን ስራ በአይነቱ አዲስ ነው። (52፡15)

- የኢሳይያስን ትንቢት መልዕክት ስንጠቀልለው ታዲያ፡ ክርስቶስ ከኃጢያት ንፁህ መሆኑን ተከትሎ በራሱ ኃጢያት አልሞተም። የሞተው በሰዎች ምትክነት ነበረ። ይህም የኃጢያት መስዋዕት ማቅረቡን የሚያመለክት ነው። ይህም ይሆን ዘንድ የአብ ፈቃድ ነበረ፤ ልጁም ተገዶ ሳይሆን በፈቃዱ የፈፀመው ብቻ ነው። በዚህም በማዳን ስራ ውስጥ በአብ ና በወልድ መካከል የነበረውን የሃሳብ ስምምነት ኢሳይያስ ያረጋግጥልናል።

በተጨማሪም ክርስቶስ የሐጢያኞችን በደል ተሸከመ ሲል ኢሳይያስ የተጠቀመው ቃል ከላይ በዘሌዋውያን 16፡22 ላይ ካየነው ጋር ተመሳሳይ ነው። ትርጉሙም የሐጢያትን ጥፋተኝነት ብቻ ሳይሆን የሐጢያትን ቅጣት መሸከምን እንደሚያመለክት ተመልከተናል። ኢሳይያስ የሚሰቃየው መሲህ ምትካችን እንዲሁም ቅጣታችንን የሚሸከም እንደሆነ በዚህ ክፍል ይነግረናል።

# ማርቆስ 10፡45

### እንዲሁ የሰው ልጅም ሊያገለግልና ነፍሱን ለብዙዎች ቤዛ ሊሰጥ እንጂ እንዲያገለግሉት አልመጣም።

በዚህ ክፍል ላይ “ቤዛ ሊሰጥ [Ransom]” ተብሎ የተተረጎመው ቃል ***lutron*** የሚለው የግሪክ ቃል ሲሆን ስርወ-ቃሉ luo የሚል ነው። ትርጓሜውም፡ ነፃ ማውጣት፣ መልቀቅ ወይም መፍታት ማለት ነው። ክርስቶስ ነፍሱን ለብዙዎች ቤዛ ሰጥቷል። ይህም ሌሎች ምትክነቱን ቁልጭ አድርጎ ያስቀምጣል። የዚህ ክፍል ሌላው ውበት ሁለት የክርስቶስን ገፅታዎች አጣምሮ መያዙ ነው። ይህም በክፍሉ ጌታ ስለ ራሱ ሲናገር ሁለት ሃረጎችን ይጠቀማል፡ የሰው ልጅ የሚል ና አገልጋይ የሚል። “የሰው ልጅ” ሲል ጌታ ዳን7፡13-14 ጋር እየወሰደን ነው። በዚህ ክፍል ዳንኤል ኢየሱስ የሚመለክ ና የሚገለገል እንደሆነ ያስቀመጠ ቢሆንም ኢየሱስ ግን የሰው ልጅ ሊያገለግል የመጣ ነው ይላል። ይህ እንግዲህ ስለ ክርስቶስ ሁለተኛ ገፅታ የሚናገር ነው። በመጀመሪያ መምጣቱ (ትስጉት) ጌታ አገልጋይ ሆኖ የሚሰቃይ መሲህ (ኢሳ 53) ሆኖ የተገለጠ ቢሆንም በሁለተኛ መምጣቱ የሚገለገል፣ ጉልበት ሁሉ የሚንበረከክለት ሆኖ ይገለጣል።

# ማቴዎስ 26፡39

### “አባቴ፥ ቢቻልስ፥ ይህች ጽዋ ከእኔ ትለፍ”

በዚህ ክፍል ፅዋ የሚለው ቃል በመፅሀፍ ቅዱስ ምንን ያመለክታል? ይህ በግልጥ የእግዚአብሄርን ፍርድ የሚያመለክት ሆኖ በተለያዩ የመፅሀፍ ቅዱስ ክፍሎች ተገልጧል። ለምሳሌ፡ መዝ75፡8 ፣ ኢሳ51፡17 ፣ ኤር25፡15 ፣ ዕንባ 2፡16… ጽዋ የሚለው የእግዚአብሄርን ቁጣ የሚያመለክት እንደሆነ ካየን ክርስቶስ ይህን ጽዋ እንደጠጣ ማቴ26፡39 ያስተምረናል።

# ምትካዊ ቅጣት በሮሜ መፅሀፍ፡

ምትካዊ ቅጣት በማስተማር ከሮሜ መፅሀፍ በላይ ግልጥ የሆነ መፅሀፍ አይገኝም። በአጭሩ በሮሜ መፅሀፍ ውስጥ ያለውን አስተምሮ ስንጠቀልለው በዚህ መልኩ ማስቀመጥ ይቻላል፡

- ✓ ሰው ሁሉ አህዛብ ወይም አይሁድ ሳይለይ ኃጢያተኛ ነው። ህግን በመጠበቅ በእግዚአብሄር ፊት በፅድቅ መቆም የሚችል አንድስ እንኳ የለም። (3፡9-20)
- ✓ እግዚአብሄር በኃጢያት ላይ ይቆጣል፤ ኃጢያትንም ይቀጣል። (1፡18 ፤ 2፡6፣ 12)
- ✓ የኃጢያት ቅጣት ደግሞ ሞት ነው። (6፡23)
- ✓ የብሉይ ኪዳን አማኞች ኃጢያት ተገቢውን ቅጣት ሳያገኝ በትዕግስት የታለፈ ነበረ። (3፡25)

- ✓ እግዚአብሄር ፃድቅ ነው፤ ፅድቁንም ሳይለቅ ኃጢያተኛውን ያፀድቃል። (3፡26)
- ✓ እግዚአብሄር ፅድቁን ሳይለቅ ኃጢያተኛውን ለማፅደቅ ለኃጢያት ሁሉ ተገቢ ቅጣት ማስተላለፍ ይኖርበታል። (3፡25)
- ✓ የኃጢያት ሁሉ (ያለፈውም የሚመጣውም) ተገቢ ቅጣት የተላለፈው በክርስቶስ ላይ ነው። (3፡25)
- ✓ ክርስቶስ ኃጢያታችንን በመሸከም የኃጢያታችንንም ቅጣት በመቀበል የእግዚአብሄርን ቁጣ አብርዶልናል (3፡25)
- ✓ በዚህም እኛ ከእግዚአብሄር ቁጣ ድነናል። (5፡9)

# የማስተሰረያ መስዋዕት (ሮሜ 3፡25)፡

የአማርኛ መፅሀፍ ቅዱስ ትርጓሜዎቻችን ሮሜ3፡25 ላይ ማስተሰረያ ብለው የፈቱት የግሪክ ቃል ***ℏilastērion’*** ሲሆን በትርጓሜው ላይ አንዳንድ ጭቅጭቆች አሉ።

- ➢ ሲ.ኤች ዶድ እንደሚሞግቱት ቃሉ የኃጢያት ስርየትን ብቻ [Expiation] በክርስቶስ እንዳገኘን የሚናገር እንጂ ከእግዚአብሄር ቁጣ [Propitiation] ጋር የሚገናኝ ሃሳብ የለውም። ከዚህ ጋር በተያያዘ የእንግሊዘኛዎቹ የመፅሃፍ ቅዱስ ትረጉሞች RSV, NEB ቃሉን ስርየት (expiation) ብለው ተርጉመውት እናገኛለን።
- ➢ ለዚህ የሲ.ኤች ዶድ ሃሳብ መልስ ይሆን ዘንድ ሌዎን ሞሪስ የመስቀሉ ሐዋሪያዊ ስብከት የሚል መፅሀፍ አዘጋጅተዋል። በመፅሀፉ ውስጥም የግሪክ ቃሉን አጠቃቀም ከቀደሙ አይሁዳዊ ና አህዛባዊ ፅሁፎች በመፈተሸ ጥልቅ ማብራሪያ ያቀረቡ ሲሆን እሳቸው እንደደመደሙት ቃሉ የሀጢያት መወገድን ብቻ ሳይሆን የቁጣ መብረድንም የሚያመላክት እንደሆነ አሳይተዋል። የቃሉም ቀጥተኛ ትርጉም የስርየት መክደኛውን እንደሚያመለክት ይናገራሉ። ዲ.ኤ ካርሰንም ከዚህ ጋር ይስማማሉ።

የሌዎን ሞሪስ ሃሳብ በእሳቸው ዘንድ ያለ ብቻ ሳይሆን በአብዛኞቹ ምሁራንም ዘንድ በስምምነት ተቀባይነት ያለው ነው። ቃሉ በገባባቸው የመፅሀፍ ቅዱስ ክፍሎችም ተመሣሣይ ትርጉምን አዝሎ እንደሚገባ ይታያል። (1ዩሀ 2፡2፣ 4፡10 ፣ ዕብ 2፡7) የዚህ ቃል የሮሜ አገባብ አውዱም ክርስቶስ የኃጢያትን ስርየት የተቀበልንበት ብቻ ሳይሆን ከእግዚአብሄር ቁጣ የዳንበትም እንደሆነ ግልጥ ነው። ቁ. 25 የክርስቶስን ሞት ከእግዚአብሄር ቁጣ ጋር አገናኝቶ እንዳስቀመጠው ማየት ይቻላል። ስለዚህ ብዙዎቹ ምሁራን እንደሚስማሙት የግሪክ ቃሉን ትርጉም ስርየት የሚለው ብቻ ሙሉ በሙሉ አይገልፀውም። ***hilastērion*** ማለት ስርየትንም እንዲሁም ቁጣ ማብረድንም በውስጡ የሚይዝ ነው። [Expiation + Propitiation]

የአዲሱ መደበኛ ትርጉም አማርኛ መፅሀፍ ቅዱስም ቃሉ የእግዚአብሄር ቁጣ መተዉን ሊያመለክት እንደሚችል በግርጌ ማስተወሻው ገልጦታል። የህያው ቃል ትርጓሜም ይህን የቃሉን ትርጓሜ አመላክቷል።

# ሞተልን ብቻ ሳይሆን ሞትን [Substitution and Representation]

2ኛ ቆሮንቶስ 5፡21 ይህን እውነት በድንቅ መልኩ ያስቀምጠዋል፡ **እኛ በእርሱ ሆነን የእግዚአብሔር ጽድቅ እንሆን ዘንድ ኃጢአት ያላወቀውን እርሱን ስለ እኛ ኃጢአት አደረገው።**

በዚህ ክፍል ውስጥ የምናገኘው የክርስቶስን ሁለት ገፅታዎች ነው፡

i. "ስለ እኛ" [for us]-- የሚለው ምትክነቱን (substitution) ያሳያል። ግሪኩ 'hyper' የሚለውን ቃል ይጠቀማል። በአጠቃላይ በእኛ ቦታ የሚለውን ትርጉም ይይዛል።
ii. "በእርሱ ሆነን" [in Him] -- የሚለው ወኪል (representative) መሆኑን ያመለክታል። የክርስቶስ ሞት ለእኛ ለአማኞች እንዴት ሊቆጠር ይችላል? ምክንያቱም በክርስቶስ ማመን ማለት ወደ ክርስቶስ መግባት ከእርሱ ጋር መዋሃድ [Union with Christ] ስለሆነ!! ከእርሱ ጋር መዋሃድ (በእርሱ መሆን) እርሱ የእኛ እውነተኛ ወኪል እንደሆነ ያሳየናል። እርሱ የሚያደርገው ሁሉ እኛ እንዳደረግነው ይቆጠራል። ሲሞት እኛ እንደሞትን ፤ ሲነሳ እኛ እንደተነሳን፤ በአብ ቀኝ ሲቀመጥ እኛ እንደተቀመጥን ይቆጠራል። (ሮሜ6፡4-5፣ ቆላ3፡1-3፣ ኤፌ3፡6) ምክንያቱም እኛ ክርስቶስ ውስጥ ነን፤ እርሱም የእኛ ትክክለኛ ተወካይ ነው።

ከዚህ እንደምናየው የክርስቶስ ሞት ምትክ ብቻ ሳይሆን አካታችም [exclusive +inclusive] ነው። መፅሀፍ ቅዱስ ክርስቶስ ለእኛ ሞተ ብቻ ሳይሆን እኛም ከክርስቶስ ጋር ሞትን ይላል። ይህም ማለት የክርስቶስ ሞት ለእኛ ይቆጠራል። (ገላ2፡20፣ ቆላ 2፡20)

- **ክርስትና ማለትም ይህ ነው፡ <u>እርሱ ስለ እኛ</u> (ምትክነት) ፤ <u>እኛ ደግሞ በእርሱ</u> (ወኪልነት) ከዚያም <u>እርሱ በእኛ</u> (ቅድስና፣ ወኪልነት፣ ክብር..)!!!**

# ክፍል-4

## ምትካዊ ቅጣት ቤዝሆት ቲዎሪ ላይ የሚቀርቡ ትችቶች ና መልሶቻቸው፡

የምትከዊ ቅጣት ቤዝሆት ተቃዋሚዎች ብዙ ጊዜ የሚያደርጉት ሃሳቡን መፅሀፍ ቅዱሳዊ በሆነ ማስረጃ ከመሞገት ይልቅ ስሜትን በሚነኩ ና በሚያሸማቅቁ ቃላት ዶክትሪኑን መግለጥ ነው። ለዚህ ስራቸው ደግሞ ያለ ጥንቃቄ ዶክትሪኑን የሚያስተምሩ ሰዎች ጥሩ ግብዐት ሆነው ይረዷቸዋል። ከሚጠቀሙባቸው ስሜታዊ መንገዶች አንዳንዶቹ የአብን ፍትህ ና ቁጣ ቅዱስ መሆኑን መካድ፣ ቁጣውን ከሰዎች ቁጣ ጋር ተመሳሳይ አድርጎ መውሰድ፣ መስቀሉን የእግዚአብሄር ፍትህ ብቻ እንደረካበት እንጂ የእግዚአብሄር ፍቅር እንደተገለጠበት የማናሳይ መሆኑን በውሸት መናገር.. በአጠቃላይ አብዛኞቹ ምትካዊ ቅጣት ቤዝሆት ተቃዋሚዎች ዶክትሪኑ የማይለውን በማለት ና እነርሱ ወደሚፈልጉት ወጥመድ እንዲገባላቸው በመጠምዘዝ የሚያቀርቡ ናቸው። ስለዚህ አላማቸው ዶክትሪኑ ላይ የስሜት ሸክም ከምረውበት ሰዎችን አሳፍሮ ማስወጣት እንጂ ሰዎችን በትክክለኛ ሙግት ማሳመን አይደለም። ይህ ማለት ግን በትክክል የሚቀርቡ ሙግቶች የሉም ማለትም አይደለም።

እስቲ አንዳንድ የሚቀርቡ ሙግቶችን እንይ፡ በዋናነት የክርስቶስ አሸናፊነት ቲዎሪን የሚቀበሉ አንዳንድ ኦርቶዶክሳውያን የሚያነሱትን ሙግቶች ለማግኘት በግሌ እጅግ በማከብራቸው ዲያቆን ያረጋል ያበጋዝ በተፃፈው መድሎተ- ፅድቅ መፅሀፍ ውስጥ የተካተቱ ሙግቶችን ላንሳ ና መልስ ለመስጠት ልሞክር፡

1. የምዕራባውያኑ ሃሳብ ከሥነ-ሕግ እሳቤ ና ድባብ የመነጩ ናቸው (ገፅ.79)
2. የፕሮቴስታንቱ የመዳን ትምህርት እግዚአብሄር በእኛ ስላደረገው ና ስለሚያደርገው ሳይሆን እግዚአብሄር ለእኛ ያደረገው ነገር ላይ ብቻ የተወሰነ ና የተገደበ ጎደሎ ነበር (ገፅ 79)
3. የቅድስት ሥላሴን ፈቃድ የሚነጣጥል ና የሚቃረን ሃሳብ ነው (ገፅ 79)
4. ኦርቶዶክሳውያን አበው የወልድ መስዋዕት የአብ ቁጣን ለማብረድ የግድ መቅረብ የሚገባው ነገር ነበረ የሚለውን የስኮላስቲሲዝም መሠረታዊ መነሻ ና ማጠንጠኛ አስተሳሰባቸውን አይቀበሉትም (ገፅ 80)
5. አብን ተለማኝ ወልድን ደግሞ ማራቸው ባይ (ለማኝ፣ ማላጅ) አድርጎ የማሰቡ ፕሮቴስታንታዊ ባህል ነው (ገፅ 80)

መድሎተ ፅድቅ የሚያነሳቸው እነዚህ ሙግቶች አንዳንዶቹ ትምህርቱ የማይለውን አለ ብለው የሚያቀርቡ ና የሃሰት መረጃ የሚያቀርቡ ናቸው። ለምሳሌ፡ ሙግት (2) መልስ እንኳን እስከማያስፈልገው ድረስ ፕሮቴስታንቱ ላይ የተነገረ ውሸት ነው። ሙግት (3) ቅድሥት ስላሴን ምትካዊ ቤዝዎት ይነጣጥላል

የሚለውም አቀራረብ ጠቅላላውን የምትካዊ ቤዝዎት አስተምሮ የሚሞግት አይደለም። የቀረበበትም መንገድ በዚህ ቲዎሪ ላይ ያሉ ሁለት ምልከታዎችን ያላማከለ ነው። ይህን በቦታው አሳያለሁ። ሙግት (5) አበው ይህን ቲዎሪ አይቀበሉትም ብለው ያቀረቡትም የሃሰት መረጃ ነው። ከዚህ በፊት እንዳየነውም አበው በዚህ ጉዳይ ላይ የተለያየ አመለካከት እንጂ ወጥ የሆነ አቋም እንደሌላቸው ይልቁንስ በርካታ መልክ ያለው የቤዝሆት ፅንሰ-ሃሳብ እንደነበራቸው አይተናል። ከሚያነሷቸውም ቲዎሪዎች ውስጥ አንዱ የምትካዊ ቤዝሆት ቲዎሪ ነው የሚለውን ተመልክተናል።

ከዚህ ቀጥለን መልስ የሚፈልጉ ነጥቦችን እንመልከት፡

## 1. የምዕራባውያኑ ሃሳብ ከሥነ-ሕግ እሳቤ ና ድባብ የመነጩ ናቸው (ገፅ.79)

መድሎተ ፅድቅ የምዕራባውያኑን የህግ እሳቤ ደጋግሞ የሚወቅስ መፅሃፍ ሲሆን ነገርግን ይህ የህግ እሳቤ መፅሀፍ ቅዱስ ላይ የሌለ መሆኑን ለማሳየት የደፈረ መፅሀፍ አይደለም። የህግ ቋንቋ መፅሃፍ ቅዱስ ላይ ጳውሎሳዊ ነው። ጳውሎስ ፅድቅን ደጋግሞ የሚያቀርበው በሥነ-ህግ ቋንቋ ሆኖ ሳለ የህግ ቋንቋን ምዕራባውያኑ ከባህላቸው ቀዱት ማለት አንችልም። በተጨማሪም ኃጢያት በመሠረታዊ ትርጉሙ የእግዚአብሄርን ህግ መተላለፍ እንደሆነ ከሐዋሪያው ዩሃንስ ጋር ከተስማማን (1ዩሀ3፡4) የኃጢያት ተጠያቂነትም ህጋዊ ይዘት ያለው መሆኑ እንዲሁም ቤዝሆትም ቢሆን በመጀመሪያ ገፅታው ህጋዊ ይዘት እንደሚኖረው ማየት እንችላለን። መድሎተ ፅድቅ ላይ መታየት የነበረበት "የህግ እሳቤ" መፅሃፍ ቅዱሳዊ አለመሆኑ እንጂ ምዕራባዊ መሆኑ አልነበረም። ይህ ግን አልተደረገም።

## 2. ምትካዊ ቅጣት ቤዝሆት ና ቅድስት ሥላሴ፡

ምትካዊ ቅጣት ቤዝሆት የማይቀበሉ ሰዎች ከሚያነሷቸው ሙግቶች ቀዳሚው አስተምሮው ሥላሴን የሚከፋፍል ነው የሚል ነው። የእግዚአብሄርን ቁጣ ወልድ አብርዷል ማለት አብ ና ወልድን የሚለያይ ነው ይላሉ። ይህ ለምን ትክክል አይደለም?

- ✓ ይህ ትችት በአንድ በኩል የማይነጣጠል ሰራተኝነት [Inseparable operation] የምንለውን የነገረ ስላሴ መሠረታዊ አስተምሮ ያልጠበቀ ነው። አብ፣ ወልድ ና መንፈስ ቅዱስ በየትኛውም መለኮታዊ ስራ ላይ ለምሳሌ ፍጥረት፣ ቤዝሆት… ወዘተ ሳይነጣጠሉ የሚሰሩ ናቸው። በሥላሴ መካከል አንድ ፈቃድ ብቻ መኖሩን ተከትሎ የሃሳብ መለያየት የሚታሰብ አይደለም። አብ የፈቀደውን ወልድ ሲከለክል ወይም መንፈስ ቅዱስ የፈቀደውን አብ ሲከለክል አናይም። ይህ ሲባል ግን አንድ አምላክ በሦስት አካላት ውስጥ መገለጡን የሚክድም አይደለም። ሥላሴ በአንድ መለኮታዊ ስራ ውስጥ በአንድ ፈቃድ በተለያየ ሚና የሚሰሩ መሆናቸውንም የዘነጋ አይደለም። ለምሳሌ፡ በቤዝሆት ስራ ውስጥ ሰው የሆነው ወልድ እንጂ አብ ወይም መንፈስ ቅዱስ አይደሉም። ሰው መሆኑ ላይ ግን የአብ፣ የወልድ ና የመንፈስ ቅዱስ ፈቃድ አንድ ነው።
- ✓ የክርስቶስ ሞትም ይህን የጠበቀ ነው። የሞተው ወልድ እንጂ አብ ወይም መንፈስ ቅዱስ አይደሉም። ነገርግን መሞቱ የአብ፣ የወልድ ና የመንፈስ ቅዱስ ፈቃድ ነው። በቅጣት ምትክነት

መሠረት በማዳን ውስጥ ወልድ ያለው ሚና የእኛን ኃጢያት መሸከም ና የእግዚአብሄርን ቁጣ ማብረድ ነው። **አብት ልጁን ያለ ፈቃዱ ወደ መስቀል አላወጣውም፤ ልጅም አባት ሳይፈልግ ይቅርታን እንዲሰጥ አላስገደደውም።** በሁለቱ መካከል የፈቃድ ልዩነት የለምና። ቅጣት ምትክነት ቤዝሆት አብ ና ወልድ በቤዝሆት ስራ ላይ የወሰዱትን የተለያየ ሚና የሚያሳይ እንጂ ሁለቱን የሚነጣጥል አይደለም። ከዚህ እንደምናየው መስቀሉ ላይ አብ ና ወልድ ተነጣጥለዋል የሚል ትችት አግባብ የሌለው መሆኑን ነው።

አብ ልጁን ልኳል፣ ይሞትም ዘንድ ፈቃድ ሰጥቷል (ኢሳ53፡10)፣ እንዲሞትም አድርጓል (ዘካ13፡7) .. ይህ ሁሉ ግን ወልድ በአብ ተገዶ የተፈፀመበት ሳይሆን ወልድ ራሱን በፈቃዱ ሰጥቶ የፈፀመው ነው። (ዕብ 10፡5-10) **መስቀሉ ይቅርታን መስጠት ያለወደደ አባት በልጅ የተለመነበት ወይም መሞት ያልፈለገ ልጅ በአባት የተገደደበት አይደለም።**

ትክክለኛ የቅጣት ምትክነት አገላለጥ በፍፁም አብ ና ወልድን አይነጣጥልም። ለምሳሌ፡ ወልድ ከአብ አዳነን፤ አብ ሊፈርድብን ሲል ወልድ ደረሰልን የሚሉ አገላለጦች ወደ ስህተት የሚያመሩ ናቸው ፤ ከምትካዊ ቅጣት ቤዝሆት አስተምሮም በቀላሉ ሊያስወጡን ይችላሉ። ምትካዊ ቅጣትን ከዘፀዐት 12 የፋሲካው በግ ስናጠና እንዳየነው የግብፅን አማልክት የመታውም ሆነ የእስራኤልን በኩር ሳይመታ ያለፈው አንዱ አምላክ እንደሆነ አይተናል። ስለዚህ

- ❖ የቅጣት ምትክነት ቤዝሆት የሚለው ይህን ነው፡ **እግዚአብሄር (ሥላሴ) በክርስቶስ ከራሱ ቁጣ አድኖናል።** ታዲያ ይህ አብን ና ወልድን ይከፋፍላል? በጭራሽ!! እንደውም የሥላሴን የፈቃድ አንድነት ጎልቶ የሚያወጣ የመፅሀፍ ቅዱስ ትምህርት ነው።
- ❖ ቁጣ የአብ ባህርይ ብቻ አይደለም። ከዚህ በፊትም እንዳየነው የእግዚአብሄር ቁጣ ከቅድስናው የሚወጣ ነው። አብ ቅዱስ ነው፤ ወልድ ቅዱስ ነው፤ መንፈስ ቅዱስ ቅዱስ ነው። ስለዚህ በኃጢያት ላይ የሚቆጣ አብ ብቻ አይደለም። ወልድም መንፈስ ቅዱስም ናቸው እንጂ። ቁጣው የጋራ እንደሆነ ሁሉ ማዳኑም የጋራ ነው። አብ አዳኛችን ነው፤ ወልድ አዳኛችን ነው፤ መንፈስ ቅዱስም አዳኛችን ነው። ይህ ሥላሴን ይከፋፍላል እንዴት ሊባል ይችላል?

በዚህ ላይ በምትካዊ ቅጣት ውስጥ ያሉ ሁለት አይነት ምልከታዎችን ልናስቀምጥ እንችላለን፡ የመጀመሪያው "እግዚአብሄር ክርስቶስን ቀጣው" የሚለውን የማይቀበሉ ናቸው። በዚህ ሃሳብ መሠረት ክርስቶስ በመስቀሉ በእኛ ላይ ቢሆን ኖሮ ቅጣት የሚሆነውን መከራ በፈቃዱ ተቀበለ እንጂ ከእግዚአብሄር ዘንድ የተቀበለው ቁጣ የለም ይላሉ። ለምሳሌ ይህን ሃሳብ ከሚቀበሉት አንዱ የሆኑት ጆን ስቶት ሲፅፉ፡ "We must never make Christ the object of God's punishment"[34] በማለት አስቀምጠዋል። በአብዛኛው ዘንድ ተቀባይነት ያለው ምልከታ ግን የእግዚአብሄር ፍርድ ይሟላ ዘንድ ክርስቶስ ከእግዚአብሄር ዘንድ የሆነውን ቁጣ መቀበል አለበት የሚለው ምልከታ ነው።ከዚህ እንደምናየው የመድሎተ ፅድቅ ሙግት የሚሰራው ለምትካዊ ቤዝዎት ጠቅላላ ሃሳብ ሳይሆን ለሁለተኛው ምልከታ ብቻ

[34] The cross of christ

ነው። ነገርግን አስተውለን ከተመለከትነው በሁለቱም ምልከታዎች ውስጥ ትምህርተ- ሥላሴ በጥንቃቄ ተጠብቆ ይገኛል። ይህም፡

- ✓ በመጀመሪያው ምልከታ ውስጥ እግዚአብሄር ክርስቶስን ቀጣው የሚለው ሃሳብ ስለሌለበት የቅድስት-ሥላሴ አስተምሮ የተጠበቀ እንደሆነ ሁሉም ይስማማል።
- ✓ በሁለተኛው ምልከታ ውስጥ እግዚአብሄር ክርስቶስን ቀጣው ስንል አንዱ የስላሴ አካል ሌላው ላይ የሚሰራው ስራ ያደርገዋልና ትምህርተ- ሥላሴን ያበላሻል የሚል ትችት ሊሰነዘር ይችላል። ነገርግን ሙግቱ አሁንም እንዲከሽፍ የሚያደርገው በትምህርተ-ሥላሴ ውስጥ የምናውቀው ኢ-ተመጣጣኝ [asymmetrical] ስራ ነው። ይህም አብ በወልድ ላይ የሚሰራው፣ ወልድ በመንፈስ ቅዱስ ላይ የሚሰራው ነገርግን በተገላቢጦሹ እውነት ያልሆኑ ብዙ ነገሮች አሉ። ለምሳሌ፡ አብ ወልድ ልኳል! አብ ላኪ ነው[subject]፤ ወልድ ተላኪ[object] ነው። ይህ እንግዲህ አብ ወልድ ላይ የሚሰራው እንደሆነ ተደርጎ ቀርቧል። ስለዚህ አብ ክርስቶስን ቀጣው የሚለው አብ ክርስቶስ ላይ የሚሰራው ስራ ነውና ትምህርተ-ሥላሴን ያፈርሳል ማለት አንችልም። ይህ ሊሆን የሚችለው ክርስቶስ ያለ ፈቃዱ የሚያደርገው ቢሆን ነበረ። ይህ ደግሞ እንዳልሆነ አይተናል።

የመድሎተ ፅድቅ ሙግት (5) ብዬ ያስቀመጥኩትም ቢሆን በዚህ ውስጥ መመለስ የሚችል ነው። ምትካዊ ቅጣት መድሎተ ፅድቅ ባስቀመጠበት መልኩ አብን ተለማኝ ወልድ ለማኝ አድርጎ አያስቀምጥም። ልመና የሚለው ቃል በራሱ ፈቃድን ለማስቀየር የሚደረግ ሙከራን የሚያሳይ ነው። በዚህ መነፅር አብ የኃጢያት ይቅርታን ለመስጠት በወልድ አልተለመነም። ማዳን ከመጀመሪያውም የአብ ፈቃድ ነው፤ መስቀሉ የአብ እቅድ ነው። እንደዚህ ሆኖ ሳለ ካልተለመንኩ ይቅርታ አላደርግም አብ ሊል ይችላል? በጭራሽ!! መስቀሉ ወደ አብ የተደረገ ልመና ሳይሆን የእግዚአብሄር ፍትህ የተሟላበት ና ፍቅሩ የተገለጠበት ነው።

በመቀጠል ከመድሎተ ፅድቅ ውጪ በተለያዩ ቡድኖች የሚነሱ ሙግቶችን እያነሳን እንመልስ፡

## 3. ምትካዊ ቅጣት እግዚአብሄር ልጁን የበዘበዘበት (Cosmic child abuse) ነውን?

አንዳንድ ሰዎች የቅጣት ምትክነትን መቀበል እግዚአብሄር ልጁን በዝብዟል እንደማለት ነው ይላሉ። ከእዚህ ጋር አያይዘው ይህ የአናሳዎችን [Minorities] መጎዳት የሚያበረታታ ነው ይላሉ። ይህን ሙግት ከሚያቀርቡ አብዛኞቹ ፌሚኒስት የሚባሉት ሲሆኑ ሌሎች ግን ምትካዊ ቅጣት ቲዎሪን ጠል የሆኑ ሆነው ለሃሳባቸው ስሜታዊ ክብደት ለመስጠት የሚጠቀሙበት ናቸው።

ይህን ለመመለስ አስቀድመን ብዝበዛ ምንድነው የሚለውን እንመልከት፡ ብዝበዛ የምንለው ያለ ልጅ ፈቃድ (በግዳጅ) ና ለበዝባዡ ጥቅም የሚደረግ ጥቃት ነው። ይህን ወስደን ከምትካዊ ቅጣት ጋር ማገናኘት እንችላለን? በጭራሽ ! ምክንያቱም፡

I. ከላይ እንዳየነው ይህም በትምህርተ ስላሴ ውስጥ የምናገኘውን የማይነጣጠል ሰራተኝነት ያማከለ አይደለም። አብ፣ ወልድ ና መንፈስ ቅዱስ በየትኛውም ስራ ላይ በማይነጣጠል መልኩ ይሰራሉ።

በፍጥረት ውስጥ፣ በማዳን ውስጥ..ወዘተ አብ ወይም ወልድ ወይም መንፈስ ቅዱስ ለብቻቸው የሚሰሩት ወይም የአንዱ ብቻ ስራ የሆነ ነገር የለም። በአንድ ስራ ውስጥ ስላሴ የተለያየ ሚና ይይዛሉ እንጂ የተለያየ ስራ አይዙም። የማዳን ስራ የአብ፣ የወልድ ና የመንፈስ ቅዱስ ነው። በዚህም አብ አለምን ለማዳን ልጁን በዘበዘ እንዴት ማለት ይቻላል? በቤዝሆት ውስጥ ቅድስት ሥላሴ በማይነጣጠል መልኩ፡

- ✓ አባት ልጁን ሰጠ
- ✓ ልጅ ራሱን ሰጠ
- ✓ መንፈስ ቅዱስ ይህን በልባችን ያውጃል፤ ይገልጣል

II. መስቀሉ ልጅ ሳያውቅ ና ሳይገባው የሄደበት ሳይሆን በሙሉ ፈቃድ የተቀበለው ነው። ጌታችን ወደ መስቀሉ ሲሄድ ምን ሊገጥመው እንደሚችል በሚገባ ጠንቅቆ ያውቃል። ወደ ምድር የመጣበትም ምክንያት ስለ ኃጢያተኞች ይሞት ዘንድ እንደሆነ ለደቀ-መዛሙርቱ ደጋግሞ ይነግራቸው ነበረ። በዚህ ላይ ጄ.ቢ. ሬሜንስናይደር እንዳብራሩት ክርስቶስ በሁለት አይነት መንገድ ስለ ራሱ ለደቀመዛሙርቱ ይነግራቸው ነበረ። የመጀመሪያው በተዘዋዋሪ መንገድ ማለትም መሲሁ መሆኑን በማሳየት ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ በቀጥታ በመናገር (ማር8፡33) ነው[35]።

III. መስቀሉ አብ ልጁን ያከብርበት ዘንድ ያቀደው ነው። የልጁን የመስቀል ሞት በሚመለከት በሰማይ ያለው ዝማሬ “ተጎድተሃል ና ሃዘኔታ ይገባሃል” ሳይሆን “ታርደሃል ና ክብር ይገባሃል” ነው። መስቀሉ ልጁ ከምንም በላይ ከፍ ከፍ የተደረገበት መሆኑን መዘንጋት የለብንም። ይህን ስንመለከት አብ ልጁን በዘበዘ ማለት ለአዕምሮ እንኳን የሚሰቀጥጥ ትልቅ ውሸት እንደሆነ እናያለን። ምትካዊ ቅጣት ቤዝሆትም ከዚህ የራቀ ነው።

## 4. ምትካዊ ቅጣት ቤዝሆት እግዚአብሄር ፍቅር እንሆነ ይዘነጋል፡

ይህን ክስ ለሚያነሱ ሰዎች የመጀመሪያ ጥያቄያችን ‘ፍቅር ማለት ምን ማለት ነው?’ የሚል መሆን አለበት። ምክንያቱም ፍቅር ምን እንደሆነ ያልገባው ሰው ካልሆነ በቀር ይህን ጥያቄ የሚያነሳ መኖር የለበትም። የእግዚአብሄር ፍቅር ምንድነው? ለሚለው ቻርልስ ሆጅ ጥሩ ምላሽ አላቸው፡ “It is true God is love. But it is no less true that love in God is not a weakness, impelling him to do what ought not to be done. If sin ought to be punished, as conscience and the word of God declare, then there is nothing in God which impels him to leave it unpunished. His whole nature is indeed harmonious, but it has the harmony of moral excellence.”[36]

ፍቅር ማለት ሁሉን መውደድ ማለት አይደለም። ጳውሎስ እንዳለውም እውነተኛ ፍቅር የሚገለጠው ቅዱሱን በመውደድ ኃጢያቱን በመጥላት ነው (ሮሜ12፡9)። እግዚአብሄር ፍቅር ነው ስንል ቅድስናውን ወይም ፍትሁን ጥሎ አይደለም። እነዚህ ባህርያቱን ከጣለ እግዚአብሄር ሲጀምርም እግዚአብሄር ባለሆነ ነበረ። ይልቁንስ እጅግ ስለሚወደን እኛ ላይ መፍሰስ የነበረበትን ቁጣ ራሱ ተቀበለው። እግዚአብሄር የእኛን

[35] The Atonement and Modern thought
[36] Charles Hodge, Systematic Theology

ኃጢያት ቅጣት ራሱ ተቀብሎ ፍቅሩን ገለጠልን፤ የራሱን ቅድስና አሳየ። በሌላ መንገድ ካቀረብነው **በፍቅሩ ምክንያት ፃድቁ እግዚአብሄር ፅድቁን ሳይተው አፀደቀን።**

*ምትካዊ ቅጣት ከምንም በላይ እግዚአብሄር ፍትሁን ያልጣለ ፍቅር እንደሆነ ያሰየናል።* ክርስቶስ ራሱ ንፁህ እንደሆነ ያውቃል፤ ንፁህ የእግዚአብሄር በግ ነው። ነገርግን የአለምን ኃጢያት ሁሉ ለመሸከም ፈቃዱን ሰጠ። ለመሞት ያውም የመስቀል ሞትን ለመሞት ፈቃደኛ ሆነ። አብ ደግሞ ልጁን ያውም አንድያ ልጁን ለሞት አሳልፎ ሰጠ። የኃጢያታችን ና የክህደታችን ፍርድ መቀበል የሚገባን እኛ ብንሆንም እግዚአብሄር ስጋን ለብሶ <u>የራሱን ቁጣ ራሱ ተቀበለ፤ ፍርዱን አስወገደው።</u> ከዚያም እንዲህ ተባለ፡ ***እንግዲህ በክርስቶስ ኢየሱስ ላሉት አሁን ኵነኔ የለባቸውም።*** የት ሄደ ኩነኔው? ብንል ***እግዚአብሔር የገዛ ልጁን በኃጢአተኛ ሥጋ ምሳሌ በኃጢአትም ምክንያት ልኮ አድርጎአልና፤ ..የሕግ ትእዛዝ ይፈጸም ዘንድ ኃጢአትን በሥጋ ኰነነ።*** ይለናል ሐዋሪያው!!! እኛም ነፃ ተባልን። ከዚህ እንደምናየው **ምትካዊ ቅጣት ቤዝሆት የእግዚአብሄርን ፍቅር የሚገልጥ ብቻ ሳይሆን እግዚአብሄርንም እንድንወደው የሚያደርገን ነው።**

ማስተዋል ያለብን ክርስቶስ የእግዚአብሄርን ቁጣ አብርዷል ስንል **በክርስቶስ እግዚአብሄር ሰዎችን ከመቆጣት ወደ መውደድ መቷል እያልን አይደለም።** ጆን ሙሬይ ይህን በጥሩ መንገድ ገልፀውታል፡ propitiation is not a turning of the wrath of God into love. The propitiation of the divine wrath, effected in the expiatory work of Christ, is the provision of God's eternal and unchangeable love, so that through the propitiation of his own wrath that love may realize its purpose in a way that is consonant with and to the glory of the dictates of his holiness. It is one thing to say that the wrathful God is made loving. That would be entirely false. It is another thing to say the wrathful God is loving. That is profoundly true. But it is also true that the wrath by which he is wrathful is propitiated through the cross. This propitiation is the fruit of the divine love that provided it.[37]

በክርስቶስ እግዚአብሄር ፍቅሩን ገለጠ እንጂ ወደ ማፍቀር አልመጣም። መስቀሉ የፍቅሩ ውጤት እንጂ የፍቅሩ ምንጭ አይደለም። በዚህ መሠረት እግዚአብሄር ከእኛ ጋር ታርቋል ስንል እግዚአብሄር ከጥላቻ ወደ ፍቅር መቷል ወይም የባህርይ ለውጥ አድርጓል እያልን ሳይሆን በነፃነት በመካከላችን ይገኝ ዘንድ ከሚወደን ከእኛ ጋር ህብረት ያደርግ ዘንድ እንዳይችል ያደረገው የእኛ ኃጢያት ተወግዷል እያልን ነው። ማለትም ቁጣው ከእኛ ላይ ተነስቷል። በጄ.ቢ. ሬሜንስናይደር በጥሩ ቃል አስቀምጠውታል፡ It is not, in deed, that God has changed in His essential nature, but He has changed in this that His love is able actively to assert itself instead of His justice.[38]

## 5. ምትካዊ ቅጣት ቲዎሪ 'ኢየሱስ በአምላኩ ተተወ' ይላል

---

[37] Redemption accomplished and applied by John Murray

[38] Atonement and modern thought p.92

“በአምላኩ ተተወ” የሚለው ገለፃ የምትካዊ ቅጣት ቲዎሪ የወለደው ሃሳብ ሳይሆን የወንጌል ፀሃፍያኑ ሃሳብ እንደሆነ እንይ፡

ማቴ 27፡46 ላይ ኢየሱስ እንዲህ ብሎ ይናገራል፡***በዘጠኝ ሰዓትም ኢየሱስ፦ ኤሎሂ ኤሎሂ ላማ ሰበቅታኒ? ብሎ በታላቅ ድምፅ ጮኸ። ይህም። አምላኬ አምላኬ፥ ስለ ምን ተውኸኝ? ማለት ነው።*** ይህ ምን ማለት ነው የሚለውን አንዳንዶች ሲያብራሩት ኢየሱስ የተተወ መሰለው እንጂ በእርግጥ አልተተወም ይላሉ። ይህን ግን ጥሩ አተረጓጎም አይደለም። ምክንያቱም ክርስቶስ በመስቀል ላይ እምነቱን አጥቶ ነበረ ወደሚለው ይወስደናል። ይልቁንስ ትክክለኛው አተረጓጎምን ለማግኘት መፍትሄው ክርስቶስ ይህን ወደጠቀሰበት ወደ መዝሙር 22 መሄድ ና የክፍሉን አውድ ማጥናት ነው። መዝሙር 22 የሰቆቃ መዝሙር ከምንላቸው የሚመደብ ነው(ቁ. 1፣ 17..)። ነገርግን የእምነት መዝሙርም ነው (ቁ.9፣ 24፣ ..)። በመዝሙሩ ዘማሪው በሚደርስበት መከራ ውስጥ ያለውን የጠነከረ እምነት እንመለከታለን። ስለዚህ ከዚህ በመነሳት ጌታ ኢየሱስ እምነት በማጣቱ ይህን እንዳልተናገረ ይልቁንስ መዝሙሩ በተፃፈበት አውድ ታላቅ እምነትን የሚያመለክት እንደሆነ ማየት ይቻላል። ማቴዎስ ምን እያለን ይሆን?

ማቴዎስ ከዚህ ክፍል ከፍ ብሎ በምድር ላይ ጨለማ መሆኑን በቁ.45 ላይ ከነገረን በኋላ ጨለማውን በቁ.46 ላይ አያይዞት የምናገኘው ከክርስቶስ መተው ጋር ነው። ጨለማ በመፅሃፍ ቅዱስ ከእግዚአብሄር ፍርድ ጋር ተያይዞ ይቀመጣል። (ኢሳ13፡9-11፣ አሞፅ5፡18) የሁለቱ ቁጥሮች ተከታትሎ መምጣት እውነትም የእግዚብሄር ፍርድ በክርስቶስ ላይ እንደነበረ ያሳየናል። በተጨማሪም ይህ የኢየሱስ ቃል ጳውሎስ ና የእብራውያን ፀሃፊ ከሚያቀርቡልን አውድ ማለትም የኢየሱስ የኃጢያት መስዋዕት ሆኖ መሞት ጋር አገናኝተን ስንፈታው ኢየሱስ የአለምን ኃጢያት በመሸከሙ ለጊዜው በአምላኩ ተትቶ እንደነበረ እንረዳለን።

ኢየሱስ በአምላኩ (ለጊዜው) ተተወ ስንል ግን ምን እያልን ነው? ለጊዜው ከሥላሴ ተነጥሎ ነበር እያልን ነው? ሥለሴ ለጊዜው ከሶስትነት ወደ ሁለትነት ቀንሰው ነበር እያልን ነው? እንደዚህ ቢሆን ኖሮ እኔም ይህ ፅሁፍ ለመፃፍ እናንተም ለማንበብ ባልታደልን ነበር። እግዚአብሄር አለምን የፈጠረ ብቻ ሳይሆን ደግፎ የሚይዝ (Necessary being) ነው። እግዚአብሄር እረፍት ቢያምረውና ቢለቀን ሞት አይደለም የሚከተለን ህላዌያችን ነው የሚጠፋው። ደጋግመን እንዳየነው ሥላሴን የሚነካ የምትካዊ ቅጣት አስተምሮ የለም። ኢየሱስ በአምላኩ ተተወ ስንል የእግዚአብሄርን ፍርድ (ቁጣ) በመስቀሉ መቀበሉን ብቻ እያመለከትን እንጂ ከሥላሴ ማንነታዊ ቦታው መውጣቱን የሚያመለክት አይደለም። የወንጌል ፀሃፊዎቹ ይህ እንዴት እንደተፈፀመ ሰፊ ማብራሪያ አይሰጡንም። ስለዚህ ያሉንን አሜን ብለን ተቀብለን በተቀረው ላይ ዝም ብንል የጠቢብ መንገድ ይሆንልናል።

## 6. ምትካዊ ቅጣት ሰዎች ለቅድስና እንዳይነሳሱ ያደርጋል፡

ይህ ምትካዊ ቅጣት ላይ ከተለመዱ ትችቶች መካከል የተለመደ ሲሆን በዋናነት ግብ ያደረገው ምትክነት የሚለው ሃሳብ ላይ ነው። ሙግት (2) ብዬ ያስቀመጥኩት የመድሎተ-ጽድቅ ሃሳብም በተወሰነ ከዚህ ጋር አብሮ የሚሄድ ነው።ክርስቶስ ምትካችን ከሆነ ቅድስና ለምን ያስፈልጋል? የእርሱን ቅድስና አንወስድም? የሚል ጥያቄ የሚያነሳም ነው። ትችቱ በአንድ አቅጣጫ ፅድቅ ና ቅድስና መካከል ያለው ልዩነት በሚመለከት ፕሮቴስታንቱ ያለውን መረዳት ያላማከለ ነው። ይህን ሃሳብ ጥርት አድርገን ለመመልከት እንዲረዳን እስቲ የሚከተለውን ላስቀምጥ፡

## DOUBLE OBIEDIENCE AND DOUBLE SATISFACTION

የክርስቶስ ማዳን (ማፅደቅ) የተመሠረተው ከጥምር መታዘዙ ና ከጥምር የማርካት ስራው ነው። ጥምር መታዘዝ ስንል ክርስቶስ በሞቱ ና በህይወቱ ሙሉ በሙሉ እግዚአብሄርን መታዘዙን እያመለከትን ሲሆን ጥምር ማርካት ስልን ደግሞ በህይወቱ ና በሞቱ የእግዚአብሄርን ህግ ና የእግዚአብሄርን ፍትህ እንዳሟላ እያመለከትን ነው። እዚህ ጋር በደንብ መረዳት ያለብን የክርስቶስ መታዘዝ በህይወቱም ሆነ በሞቱ የፈቃደኝነት ገቢር ስራው [Active obedienece] መሆኑን ነው። በተለምዶ የክርስቶስ ህይወት ገቢር ታዛዥነት (Active)፤ ሞቱ ደግሞ (Passive) ታዛዥነት እንደሆነ ይቀመጣል። ይህ ግን አገላለጥ ብቻ እንጂ ክርስቶስ ሞቱ በእርሱ ላይ ያለፈቃዱ የተሰራበት (Passive) ነው ለማለት አይደለም። ጌታም ሲናገር ***ነፍሴን ደግሞ አነሣት ዘንድ አኖራለሁና ስለዚህ አብ ይወደኛል። እኔ በፈቃዴ አኖራታለሁ እንጂ ከእኔ ማንም አይወስዳትም። ላኖራት ሥልጣን አለኝ ደግሞም ላነሣት ሥልጣን አለኝ ይህችን ትእዛዝ ከአባቴ ተቀበልሁ።***(ዩሀ10፡17-18) ብሏልና!

ጆን ሙሬይ በመፅሃፋቸው የክርስቶስ ጣምራ መታዘዝ በሚመለከት ሲያብራሩ Active obedience የሚለው በህይወቱ Passive obedience የሚለው በሞቱ የተገደበ ብቻ እንዳልሆነ ይልቁንስ Active ሲባል ክርስቶስ የእግዚአብሄርን ህግ መታዘዙን ፤ Passive ሲባል ደግሞ የኃጢያት ቅጣት መቀበሉን የሚያሳይ እንደሆነ አሳይተዋል። ከዚህ ጥምር መታዘዙ በመነሳት ጥምር መቆጠር [Double imputation] አግኝተናል። ይህም

- ✓ የክርስቶስ መታዘዝ ሁሉ ለእኛ ፅድቅ ሆኖ ተቆጥሮልናል።
- ✓ የእኛ ኃጢያት በክርስቶስ ላይ ተቆጥሮ ቅጣት ተላልፎበታል።

ከዚህ ክፍል የምንማረው አስፈላጊ ነገር ክርስቶስ ኃጢያት ሆነ ስንል የእኛን ምግባራዊ ስራዎች መሰለ እያልን ሳይሆን የኃጢያታችንን ቅጣት ተቀበለ እያልን ነው። 2ቆሮ 5:21 ላይ ብንመለከት ሃሳቡ የቀረበበትን አውድ እኛ ፃድቅ የሆነው እርሱ ኃጢያት ሆኖልን ነው የሚለውን የሚሰጠን ነው [Double imputation]። ሐዋሪያው በዚህ ክፍል **ክርስቶስ ኃጢያት ሆኖልናል ሲል የእኛን ቅጣት ተቀብሏል እያለ እንጂ በምግባር እኛን መስሏል እያለ እንዳልሆነ ሁሉ ፀድቀናል ስንል በእግዚአብሄር ፊት ጥፋተኛ አይደላችሁም ተብለናል እያልን እንጂ ክርስቶስን በምግባር መስለናል እያልን አይደለም።** እኛ በክርስቶስ ፃድቅ ሆነናል ስንል የክርስቶስን ምግባራዊ ስራዎች ወርሰናል ወይም ቁርጥ ኢየሱስን መስለናል እያልን አይደለም። ክርስቶስን መምሰል ከክርስቶስ ያለሱታፌ የምንቀበለው አይደለም።

እንደዛማ ቢሆን መንፈስ ቅዱስ ባላስፈለገን ነበረ። ክርስቶስን መምሰል ክርስቲያናዊ እድገት ነው። ስለዚህ ምትካዊ ቅጣትን በደንብ የተረዳ ሰው ክርስቶስ ምትክ ሆኖልኛል ብሎ ከቅድስና (ክርስቶስን ከመምሰል) ሊርቅ አይችልም። በክርስቶስ ያለ ሱታፌ ፀድቀናል፤ እንቀደስ ዘንድ ግን የእኛ ሱታፌ ያስፈልገናል።

ከላይ ባየነው መሠረት ደግሞ ምትካዊ ቅጣት ቤዝሆት በመስቀሉ የተገለጠውን የእግዚአብሄርን ፍቅር እንድንገነዘብ ስለሚያደርገን ና የወደደንን እግዚአብሄርንም እንድንወደው ስለሚያደርገን **ትክክለኛ የቅድስና ተነሳሽነት (እርሱም ፍቅር)** እንዲኖረንም የሚያደርግ ነው።

## 7. ምትካዊ ቅጣት በክርስቶስ ሞት ላይ ብቻ ትኩረት ያደረገ ነው፡

ይህ ክስ ውሃ የሚያነሳው ምትካዊ ቅጣት ብቻውን የሚቆም የቤዝሆት ቲዎሪ ቢሆን ነበር። ነገርግን ከዚህ በፊት እንዳየነው ሁሉን አቃፊ የሆነ ቲዎሪ ስለሆነ ከሌሎች በተሻለ መስቀሉ ላይ ማዕከል ያደረገ ነገርግን ሌሎች የክርስቶስ ስራዎችን፣ ህይወቱን ና ትንሳኤውን ባካተተ መልኩ ትክክለኛ የቤዝሆት ቲዎሪ እንዲኖረን ይረዳናል።

- ኢየሱስ ህይወቱ-- ፅድቃችን ነው፤ ምሳሌያችን ነው
- ኢየሱስ አገልግሎቱ-- ራሱን የገለጠበት፣ አለምን ና ሰይጣንን ያሸነፈበትም ነው
- ኢየሱስ ሞቱ-- የኃጢያታችን ስርየት የተቀበልንበት፤ ከቁጣ የዳንበትም ነው
- ኢየሱስ ትንሣኤው-- እርሱ እውነተኛ ጌታ መሆኑን ያወቅንበት፣ የእኛም መዳን ዕውን እንደሆነ ያየንበት፣ አብ መስዋዕቱን መቀበሉን ያረጋገጠበት ነው።

በአጠቃላይ አዳኛችን ኢየሱስ ነው!!! ኢየሱስ ያደረገውን ሁሉ ያደረገው፤ የኖረውን ሁሉ የኖረው ለድነታችን ነው። ወደ ሰማይ ሲያርግ፣ በአብ ቀኝ ሲቀመጥ ፣ መንፈስ ቅዱስን ሲልክ ሁሉ ለመዳናችን ነው።

## 8. ምትካዊ ቅጣት ለኢየሱስ የማይገባ ንግግር ያደርጋል

ኢየሱስ በመስቀሉ ተቀጣ፣ ተፈረደበት፣ ከአምላኩ ተለየ (መንፈሳዊ ሞትን ሞተ).. ወዘተ የሚሉ ቃላት ለኢየሱስ የሚመጥኑ ቃላት አይደሉም። ነገርግን ምትካዊ ቅጣት ቲዎሪ የመስቀሉን ስራ ሲገልጥ ይጠቀማቸዋል። ታዲያ ይህ ትክክል ነው?

ይህን ለመረዳት ለኢየሱስ የማይገቡ ና የማይመጥኑ የምንላቸውን ንግግሮች (ምትካዊ ቅጣት የሚጠቀማቸውን) .. “ስለ እኛ” የሚል እንጨምርባቸው፡- ኢየሱስ **ስለ እኛ** ተቀጣ፣ ኢየሱስ **ስለ እኛ** ተፈረደበት፣ ኢየሱስ **ስለ እኛ** ከአምላኩ ተለየ… ስለ ማን? ስለ እኛ!! ይህ የአምልኮ ምክንያታችን ነው። ይህ ትምህርቱን ከቲዎሎጂ ወደ ዶክሶሎጂ ይስደዋል።

# ማጠቃለያ፡

ምትካዊ ቅጣት ቲዎሪ ለብቻው የቆመ ወይም የሚቆም ቲዎሪ ሳይሆን ከሌሎች ቲዎሪዎች ጋር ሆኖ ማዕከላዊነትን በመያዝ የክርስቶስን መስቀል ስራ ይገልፃል። ይህ ቲዎሪ በመፅሀፍ ቅዱስ ና በቤተክርስቲያን አባቶችም ዘንድ ተቀባይነት የነበረው ና ያለው ለመሆኑ ማስረጃዎችን ቀርበዋል። ይህን ቲዎሪ የማይቀበሉ ሰዎችም የሚያነሷቸውን ትችቶት ተመልክተን ለመመለስ ተሞክሯል። በአጠቃላይ ይህ **ምትካዊ ቅጣት ቤዝሆት ክርስቶሳዊ ና ሥላሴያዊ ዶክትሪን ነው።**

- ✓ <u>ክርስቶሳዊ</u>፡ ክርስቶስ ሙሉ አምላክ ፤ ሙሉ ሰው ካልሆነ የሚያቀርበው መስዋዕት ተቀባይነት አይኖረውም። ሙሉ ሰው ባይሆን የእኛ ትክክለኛ ተወካይ መሆን አይችልም። ሙሉ አምላክ ባይሆን ኃጢያት አልባ መስዋዕት ና ለአለም ሁሉ የሚበቃ መስዋዕት ማቅረብ ባልቻለ ነበር።
- ✓ <u>ሥላሴያዊ</u>፡ አብ ባይኖር ክርስቶስ ባልተላከ ነበር፣ ወልድ ባይኖር አምላክ ሰው ባልሆነ ነበር፣ መንፈስ ቅዱስ ባይኖር ወልድ ሰው ባልሆነ እኛም ይህን እውነት ሳንካፈል መቅረታችን ነበረ።

በዚህ ምክንያት ምትካዊ ቅጣት ቤዝሆት መስቀሉን እንድንረዳው፣ ጌታችን የከፈለውን ዋጋ እንድናውቀው ና እንድንወደው የሚያደርገን የመፅሀፍ ቅዱስ ትምህርት ነው። እንደሚመስለኝ እንደዚህ ግልጥ የመፅሀፍ ቅዱስ ትምህርት ሆኖ ሳለ የጭቅጭቅ ሳይሆን የምስጋና ምክንያታችን መሆን የነበረበት ርዕስ ነበረ። እንዳለመታደል ሆኖ ግን ይህ እውነት የሆነው ለጥቂቶች ብቻ ነው። ጌታ ይርዳን.. ተባረኩ!!!

# REFERENCES


- Pierced for Our Transgressions: Rediscovering the Glory of Penal Substitution by Andrew Sach and Steve Jeffery
- In My Place Condemned He Stood: Celebrating the Glory of the Atonement by J.I Packer and Mark Dever
- The cross of Christ by John Stott
- The Logic of Penal Substitution by J.I packer
- Redemption, Accomplished and Applied by John Murray
- Atonement and the death of Christ by William Lane Craig
- The nature of the atonement four views by by Bruce R Reichenbach
- Vicarious Atonement by Lois Berkhof
- The Atonement Its Meaning and Significance by Leon L. Morris
- The truth of the Cross R.C. Sproul
- Theological retrieval for evangelicals by Gavin Orthlund
- Historical theology an introduction to Christian doctrine by Gregg R. Allison
- The Atonement and Modern Thought by J. B. Remensnyder
- መድሎተ ፅድቅ በዲያቆን ያረጋል ያበጋዝ